በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ በሌላ አገባብ ብንመለከተው ይን ሐቅ እንረዳለን:: ክህነትን አጽንቶ ዲያቆን ሆኖ ለመኖር ድንግልናን መጠበቅ ግድ መሆኑ ለማንም የተሠወረ አይደለም:: ስለዚህ አንድ ዲያቆን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ድንጋሌ ሥጋውን ሲያፈርስ ክህነቱን እያፈረሰ መሆኑ ግልጽ ነው:: ነገር ግን በተገቢ መንገድ ጋብቻ ፈጽሞ ሩካቤ በማድረጉ ምክንያት ድንጋሌ ሥጋውን ሲያጣ ክህነቱን ግን አያጣም:: ምክንያቱም ሕጋዊ ሩካቤ የነፍስን ድንግልና ስለማያጠፋና ስለማያረክስ ነው::

ድንጋሌ ነፍስ የሌለው ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም:: ይህም ማለት የነፍስን ድንግልና የሚያጠፋው ኃጢአት ብቻ በመሆኑ ኃጢአቱን በንስሐ ያላራቀ ወይም ንስሐ ያልገባ ሰው ወደ መንግሥተ ሰማያት አይገባም ማለት ነው:: ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእይ መጽሐፉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚችሉት የነፍስ ድንግልና ያላቸው ብቻ መሆናቸውን ሲገልጽ፡- «ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው ድንግሎች ናቸውና:: በግ ወደሚሄድበት የሚከተሉ እነዚህ ናቸው:: ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኩራት እንዲሆኑ ከሰዎች የተዋጁ እነዚህ ናቸው::» ይላል:: ራእይ14፥4

በተጨማሪም ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድንጋሌ ነፍስ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ዋና ነገር መሆኑን ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «እስመ ድንጋሌ ነፍስ ይሬሲ ሱታፌ ምስለ ክርስቶስ ወያበውእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት» ይህም በአማርኛ «ድንጋሌ ነፍስ ከመርዓዊ (ከሙሽራ) ክርስቶስ ጋራ አንድ ያደርጋል:: ወደ መንግሥተ ሰማያትም ያገባልና» ማለት ነው:: ዮሐ.ተግ.28





## «ድንግል በክልኤ»

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም «ድንግል በክልኤ» እየተባለ በቅዱሳት መጻሕፍት ተነግሮላታል:: ስለ ድንግልናዋ ትንቢት ተነግሯል ምሳሌም ተመስሏል:: ይህም በሁለት ወገን ማለትም በሥጋና በነፍስ ድንግል መሆኗን ለማመልከት ነው:: የደናግልም ሁሉ መመኪያቸው እርሷ ናት::

እመቤታችን ቅድመ ፀኒስ፣ ጊዜ ፀኒስ፣ ድኅረ ፀኒስ ድንግል ናት:: ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድም ድንግል ናት:: ቅዱሳንን ሁሉ ስለ ድንግልኗ ምስጋናና ክብር ያለ ማቋረጥ እንዲናገሩ ያደረገ ይህ ንጽሕናዋ ነው:: «ስብሐተ ድንግልናኪ ወትረ ይነግር አፉየ» እንዲል:: (መልክዐ ማርያም)

የእመቤታችንን ድንግልና «ድንግልና» በመባሉ ብቻ ካልሆነ በቀር የፍጡራን ድንግልና በምንም አይመሳሰለውም:: ስለ እመቤታችን ድንግልና ለመናገር ሌላ ትልቅ ጥራዝ ያለው መጽሐፍ መጻፍ ያስፈልጋል:: ስለድንግልና ለመናገር ስንፈልግ ስለ እርስዋ ከተጻፉት መንፈሳዊ ድርሰቶች አስረጅ አድርገን ብዙ ብንጠቅስም በድንግልና ፍጽምት ከመሆኗ የተነሣ የፍጡራንን ድንግልና ሕጹጽነት ለማየት እንዲረዳን ነው እንጂ ለማመሳሰል አይደለም::

የእመቤታችንን ድንግልና የመላእክትም ንጽሕና አይደርስበትም:: ለዚህም ማስረጃው የተአምረ ማርያም መቅድም እንዲህ ሲል ያሰፈረው ቃል ነው:: «ለመኑ ተውህበ ተደንግሎ ሕሊና እምውሉደ ሰብእ፣ ለመላእክትኒ ኢተክህሎሙ ተደንግሎ ሕሊና እስመ አበሱ በፍትወት ወወረዱ ምድረ በመዋዕል ዘቀዳሚ» በአማርኛ

እንደ ተሰጣቸው ይገልጻል:: ከዚህም በድንግልና መኖር ለጥቂቶች የሚሰጥ ጸጋ መሆኑን መረዳት ይቻላል::

ሰው ሁሉ በተሰጠው ጸጋ መኖር ይገባዋል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በድንግልና መኖር (ምንኩስና) የተሰጠው በድንግልና ጋብቻም የተሰጠው በትዳሩ ጸንቶ እንዲኖር «ወንድሞች ሆይ እያንዳንዱ በተጠራበት እንደዚህ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ይኑር::» በማለት መክሯል:: 1ቆሮ7፥24

ድንግልናን በሕይወት ዘመን በሙሉ ጠብቆ በምንኩስና መኖር ከስጦታነቱ በተጨማሪ በፈቃደኝነት ሊደረግ የሚገባው ነገር ነው እንጂ የሚገደዱበት ተግባር አይደለም:: ሐዋረያው ድንግልናዊ ኑሮ ውዴታ እንጂ ትእዛዝ አለመሆኑን ሲገልጽ «ስለ ደናግልም የጌታ ትእዛዝ የለኝም» በማለት ተናግሯል::

በድንግልና ተወስኖ ለመኖርም ሆነ ወደ ጋብቻ ለመሄድ የድንግልና መኖር አስፈላጊ በመሆኑ ድንግልናን ጠብቆ ለመኖር ስጦታችን የትኛው እንደሆነ ማወቅም አያስፈልገንም:: በድንግልና ኖረን ከመነኮስን እሰይ ያሰኛል፥ ካገባንም ይበል የሚያሰኝ ነውና ድንግልናን ከወዲሁ ጠብቆ መኖር ይገባል::

እስከ ጋብቻ ድረስ ድንግልናውን ጠብቆ ኖሮ ያገባ ሰው ሐዋርያው እንደተናገረው መልካም አደረገ:: 1ቆሮ7፥38 የታዘዘውን በሚገባ ፈጽሟልና ከበጎ ባርያዎች ጋር ይቆጠራል:: ያላገባ ወይም መላ ዘመኑን በድንግልና ለመኖር የወሰነ ደግሞ ከታዘዘው በላይ የትሩፋት ሥራ ሠርቷልና የተሻለ አደረገ:: 1ቆሮ7፥38

በጎ ሎሌን ጌታው ሽማ አጥበህ፣ ማገር ቆርጠህ ና ብሎ ያዘዋል:: እርሱ ግን ጌታዬ አይችልም በማለት አዝኖልኝ ነው እንጂ





ዓሣን ለወጥ፣ ለማገር ደግሞ ልጥ ጨምሬ ይገፍ ብሄድ ይከፋልን? ብሎ ልብሱን ካጠበና ማገሩን ከቆረጠ በኋላ ዓሣውንና ልጡን ጨምሮ ይመለሳል:: እንደዚሁ ሁሉ መነኮሳትም የፈጣሪ ታማኝ ባሪያዎች ናቸው:: ስለዚህ ፈጣሪ ሚስት አግብታችሁ፣ አሥራት፣ በኩራቱንና ቀዳምያቱን አውጥታችሁ፣ ሥጋውን ደሙን በሚገባ ተቀብላችሁ ኑሩ ቢላቸው ሚስት ማግባትን ተዉ:: ይህንንም ያደረጉት ባሕሪያቸው ደካማ ነውና አይቻላቸውም ብሎ ፈጣሪያችን አዝኖልን ነው እንጂ ከሕገ ሥጋ ሕገ ነፍስ፣ ከሕገ እንስሳ ሕገ መላእክት እንደሚበልጥ የታወቀ አይደለምን? በማለት ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ብለው በበጎ ፈቃደኝነት ነው እንጂ ተገደው አይደለም:: በዚህ ሥራቸው የተሻለ አድርገዋልና እንደ ታማኝ ሎሌ ይመሰገናሉ እንጂ አይነቀፉም:: ማቴ13፥4-8 (ትርጓሜ)

መላ ዘመንን ከሴት ርቆ ንጽሕ ጠብቆ በድንግልና መኖር በግዴታ ወይም በትእዛዝ የሚደረግ ሳይሆን ከፍቅረ እግዚአብሔር የተነሣ በፈቃደኝነት የሚደረግ መሆኑን «በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፥ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ» በማለት ጌታችን የተናገረው ቃል ያስረዳል:: ማቴ19፥12

«በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ» ማለት እንደ ኤርምያስ እና ዮሐንስ መጥምቅ ከማኅፀን ጀምሮ በምናኔ ለምንኩስናና ለድንግልዊ ኑሮ ተመርጠው የተለዩ አሉ ማለት ነው:: «በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ» እንዳለው ማለት ነው:: ኤር1፥5

«ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ» ማለት መምህራን መክረውና አስተምረው ንጹሐን ያደረጓቸው ለድንግልናዊ ኑሮ

ያበቋቸው አሉ ማለት ነው:: ለምሳሌ፦ ሙሴ ኢያሱን፣ ኤልያስ ደግሞ ኤልሳዕን ቀርጸው ለዚህ ዓይነት የመዓርግ ኑሮ አብቅተዋቸዋል::

«ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ» ማለት ፈጣሪያችን አይችሉትም በማለት አዝኖልን ነው እንጂ ሳያገቡ መኖር የተሻለ ነው በማለት በራሳቸው ፈቃድ ድንግልናቸውን ጠብቀው ከሴት ርቀው መንግሥተ ሰማያትን የሚጠባበቁ አሉ ማለት ነው::

ከላይ የተጠቀሰው ቃል በገዛ ፈቃድ በንጽሕና መኖርን የሚያመለክት እንጂ አካልን ስለ መቁረጥ የተነገረ አይደለም:: አካል ቢኖርም ሥራውን ካልሠሩበት የሌለ ያህል ነውና «ጃንደረባ» በማለት የተናገረው ስለዚህ ነው:: ንዑስ መሌሊትን (ነፍረተ አካልን) መቁረጥ ግን ከመንግሥተ ሰማያት ያወጣል፣ ከክህነትም ያሽራል::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መላ ዘመንን በድንግልና መኖር የፈቃድ ኑሮ መሆኑን ለማመልከት «ስለ ደናግልም የጌታ ትእዛዝ የለኝም» ይበል እንጂ መልካም ምክርና ለጽናት ምሳሌ የሚሆን ድንግልናዊ ኑሮ ግን አለው:: ስለዚህ «ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁ» በማለት ተናግሯል:: 1ቆሮ7፥7

ሐዋርያው ከሕይወቱ ምሳሌነት በተጨማሪ ምክሮቹ በመሉ በድንግልና መኖርን የሚያበረታቱ ነበሩ «...ከጌታ ምሕረትን የተቀበልሁ እንደ መሆኔ ምክር እመክራለሁ» ካለ በኋላ «እንግዲህ ስለ አሁኑ ችግር ይህ መልካም ይመስለኛል ሰው እንዲህ ሆኖ ቢኖር





መልካም ነው» በማለት በዘመኑ ካለው ችግር የተነሣ በድንግልና መኖር መልካም መሆኑን አስረድቷል:: 1ቆሮ7፥25-26

ሐዋርያው «ስለ አሁኑ ችግር» በማለት የተናገረው ቃል ሊሠመርበት የሚገባ ነው:: ሐዋርያው በነበረበት ዘመን ድንግልናዊ ኑሮን ከመንፈሳዊ ጠቀሜታው ባሻገር ከጋብቻ ኑሮ ይልቅ የተሻለ የሚያደጉት ብዙ ነገሮች ነበሩ:: ይህ እኛ ያለንበት ዘመን ደግሞ ከዚያን ጊዜ ይልቅ ድንግልናዊ ኑሮን የተሻለ የሚያደርጉት ችግሮች በመጠንም ሆነ በዓይነት የበረከቱበት ወቅት ነው:: ስለዚህ ምንም እንኳን መላ ዘመንን በድንግልና መኖር አስቸጋሪ መስሎ ቢታይም እስከ ጋብቻ ድረስ እንኳን ድንግልናን ጠብቆ መቆየት ከድንግልናዊ ኑሮ ጥቅሞች እንድንጋራ የሚያደርግ ነው::

## እስከ ጋብቻ ጊዜ ድረስ መደንገል

በሀገራችን በኢትዮጵያ የድንግልና ሕይወት ከጥንት አባቶቻችን ጀምሮ የተከበረና በማንኛውም ሰው ዘንድ ዋጋ ያለው ነገር ነበር:: ይኸውም ይታወቅ ዘንድ የድሮ ሰዎች ልዩ ልዩ ዘዴና ጥናት አድረገውለት ሲሠሩበት ቆይተዋል:: ማለትም አንድ ሰው ዕድሜው ወይም ችሎታውና ስሜቱ የኑሮ ደረጃውም ማግባት እስከሚፈቅድለት ድረስ በድንግልና መኖር ግዴታው ነበር:: ስለዚህ ሴቷና ወንዱ እንዳይተያዩ፣ እንዳይገናኙና እርስ በእርሳቸው ስሕተት እንዳይሠሩ በማለት በልዩ ልዩ ዘዴ ይጠበቁ ነበር::

በሀገራችን የ«ታላላቅ» ሰዎች ልጆች የተባሉት ሴቶች የሆኑ እንደሆነ በሞግዚቶችና በወላጆች እየተጠበቁ በክብር፣ በማዕርግ ያድጉ እንደ ነበር ወንዶች የሆኑ እንደሆነ ደግሞ እንደ ገዳም እንደ አምባ ያለ ከሰው የተለየ ቦታ ተሰጥቷቸው በንጽሕናና በድንግልና የያድጉ እንደ ነበር ታሪክ በሰፊው ያስረዳናል፡፡

በ«ዝቅተኛውም» ማኅበረ ሰብእ ቢሆን እንደ ዛሬ ጊዜ ሳይዘገዩ በፍጥነት ስለሚጋቡ እስከዚያው ድረስ ግን ድንግልናን ጠብቆ ለመቆየት የተቻላቸውን ሁሉ ሳያደርጉ አይቀሩም ነበር። ዛሬ ዛሬ ደግሞ እጅግ በዛ እንጂ በሁሉም ረገድ እስኪደረጁ ድረስ ሳያገቡ መዘግየቱ መልካም ሆኖ ሳለ ስለ ንጽሕናቸው አጠባበቅ ደግሞ ምንም የተወሰደ እርምጃ ስለ ሌለ የድንግልና ሕይወት እየቀለለና ዋጋ እያጣ መጥቷል። በጨቅላ ዕድሜያቸው ያገቡ ልጆች ጋብቻቸው እንደማይጸናና ችግር እያጋጠማቸው እንደ ሆነ ሁሉ ሳያገቡ ድንግልናቸውን የሚያጠፉና ስድ የለመዱ የዛሬ ተጋቢዎችም ራሳቸውን ገትቶ መያዝ ስለማይሆንላቸው ከትዳር በኋላ ሲያዝኑና ሲያለቅሱ ማየት የዘወትር ክሥተት ሆኗል። ስለዚህ ድንግልናን የመጠበቅ ጥቅም ይህ ነው ተብሎ ከሚጠቀሰው በላይ ስለሆነ የትዳር ሕይወቱን ጤናማነት የሚሻ ሁሉ ከጋብቻ በፊት ድንግልናው ሳያስደፍር መኖር ይኖርበታል።

እንደዚሁም እስራኤላውያን ከጋብቻ በፊት ድንግልና እንዳይጠፋ የሚቆጣጠሩበት ከባድ መንፈሳዊ ሕግ ፈጣሪ ሰጥቷቸው ነበር። ማለትም ከጋብቻ በፊት ድንግልናውን የሚያጠፋ ሁሉ በድንጋይ ተወግሮ፣ በእሳት ተቃጥሎ ይገደል ነበር። ዛሬ ዛሬ በአንዳንድ የሀገራችን ገጠራማ አካባቢዎች እንደሚደረገው ሁሉ በእስራኤላውያንም ዘንድ አንድ ሰው ሁነኛ የትዳር አጋሩን አግኝቶ እስከሚያገባ ድረስ ድንግልናውን ጠብቆ ይኖር ነበር። እነዚህ የታሪክ ማስረጃዎች እስከ ጋብቻ ድረስ ድንግልናን ጠብቆ መቆየት አግባብ እንደነበር ያስረዳሉ።

ወደ ጥንታዊው ግሪክ ኅይነ ልቡናችንን የመለስን እንደሆነ ደናግል ተለይተው የሚኖሩበት በዕውቀትና በሥልጣኔ ይኅለምሱበት





የነበረ ቦታ ተለይቶ «ፓርቴናጎግዮን» የሚል ስያሜ እንደነበረው እስከ አሁን ድረስ ያሉ የግንቦቹ ፍራሽና ታሪክ ያስረዳሉ።

ድንግልናን መጠበቅ ለጊዜው (እስከ ጊዜው) የሚባለው እስከ ትዳር ለማለት ነው። ከትዳር በኋላ ግን ወንዱ ድንግልናውን በክብረ ስጦታነት በረቂቅ መንገድ ለሚስቱ ሲያስረክብ ሴቲቱ ደግሞ እንደዚሁ ሕንን በግሚሥ ሊታወቅ በሚችል መልኩ (በግዘፍ) ለባሏ ትሰጣለች። ይህ ሲሆን በባልና በሚስት መካከል ጥልቅ የሆነ መከባበር፣ መተሳሰብ፣ መተማመንና መፈቃቀር ይኅለብታል።

እንደ ምንኩስና ሁሉ ጋብቻም በድንግልና ተጠብቀው ከኖሩ በኋላ ሊገባበት ይገባል። ኃብቻ እንደ ፈቀዱ በኃጢአት ሲጨማለቁ ከኖሩ በኋላ በመጨረሻ የሚፈጸም ሥርዓት አይደለም። ምንም እንኳን ደናግላን ካልሆኑ ማግባት አይቻልም ባይባልም በድንግልና ሆነው የሚፈጽሙት ጋብቻ ግን ብዙ ጸጋና በረከት አለበት። ጋብቻ በደናግላን ያምራል። የብዙ ቅዱሳን ወላጆችም በድንግልና ኖረው በቅዱስ ጋብቻ የተወሰኑ ናቸው።

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ድንግልና በተናገረበት አንቀጽ «ስለ ደናግል የጌታ ትእዛዝ የለኝም» 1ቆሮ7፥25 በማለት የተናገረው በሕይወት ዘመን በሙሉ በድንግልና ስለ መኖር ነው እንጂ እስከ ጋብቻ ጊዜ ድረስ በድንግልና ለመኖር ሥርዓትም ትእዛዝም የለም ለማለት አይደለም። እስከ ጋብቻ ጊዜ ድረስ ማንኛውም ሰው ድንግልናውን ጠብቆ የመኖር መንፈሳዊ ግዴታ አለበት።

ድንግልናን እስከ ጋብቻ ድረስ ጠብቆ ማቆየት ለሰው ልጅ በሙሉ የተሰጠ ችሎታ ነው። ስለዚህ ይህ በውዴታ መደረግ ያለበት ነገር ብቻ አይደለም። መንፈሳዊ ግዴታና ትእዛዝም እንዳለበት መታወቅ አለበት። መላ ዘመንን በድንግልና ኖሮ ለመፈጸም ግን

አስቀድሞ እንደተገለጸው መመረጥና መታደል ያስፈልጋል:: ማቴ19፥11 በዐዋጅ የተደነገጉትን አጽዋማት በተሠራላቸው ቀኖና መሠረት መጾም ለሁሉ የሚቻል ነው:: ሥርዓቱ የተሠራው የሰውን ሁሉ ዐቅም በሚያውቅ በመንፈስ ቅዱስ ነውና:: ከዚያ አብልጦ ምንም እህል ሳይቀምሱ እንደ ሙሴና እንደ ኤልያስ ለዐርባ ቀናት ለመጾም ግን መመረጥንና መታደልን ይጠይቃል:: መላ ዘመንን በድንግልና ለመኖርም እንዲሁ ሲሆን እስከ ጋብቻ በንጽሕና ለመቆየት ግን ለሰው ሁሉ የታወጀ ነው:: ዘፀ34፥28፤ 1ነገ19፥8

## በድንግልና መኖር የማይቻል ነገር ነው?

አንዳንድ ሰዎች ድንግልናን መጠበቅ የማይቻል ነገር እንደ ሆነ አድርገው ሲናገሩ ይደመጣል:: እውነት ድንግልናን መጠበቅ ይቻላል? አዎን! በደንብ ይቻላል:: የማይቻል ቢሆን ኖሮ ፈጣሪ የፈጠረውን ፍጥረት ይዘት ያውቃልና እስከ ጋብቻ ጊዜ ድረስ ድንግልናችንን እንድንጠብቅ ባላዘዘንም ነበር:: ከበሬ መራገጥን፣ ከአህያ ደግሞ መዋጋትን የሚጠብቅባቸው የለም:: ለዚህ ስላልተፈጠሩ አይቻላቸውምና:: እግዚአብሔርም ለሰው የማይቻለውን አያዘውም አይጠብቅበትም::

ሩካቤ ሥጋን እንደምንተነፍሰው አየር፣ እንደምንጠጣው ውኃና እንደምንመገበው ምግብ መቁጠር የለብንም:: ምክንያቱም እነዚህን ያጣ ሰው ብዙ ሳይቆይ ወደ ሞት ይሄዳል:: ሰው ግን ሩካቤ ባለማድረግ ብዙ ሊፈተን ይችል ይሆናል እንጂ አይሞትም:: ስለዚህ ሩካቤ ሥጋ የማይቋቋሙት ነገር አይደለምና ድንግልናን መጠበቅ ይቻላል::

ድንግልናን መጠበቅ አይቻልም በማለት የሚያምኑ ሰዎች ከግትር አቋማቸውና ከድክመታቸው የተነሣ ብዙ ደናግላንን እንደ





ምሳሌ ቢያቀርቡላቸው እንኳን አያምኑም:: ወይም ጤናማነታቸውን እንጠራጠራለን በማለት ምክንያት ይደረድራሉ:: ነገር ግን ንጽሕና መጠበቅን የመሰለ ጤናማነት የለም:: ከኃጢአት ተለይቶ ድንግልናን በመጠበቅና ነፍስን ጤናማ ማድረግ ከጤናማነትም በላይ ነው:: ጤና ማጣትስ እንደ ክፍት ቤት የዘማዊያን መናኸሪያ መሆን ነው:: ስለዚህ በአዋናባጆች አሉባልታ በመደናገጥ ጤናችንን እስከ መጠራጠር ደርሰን ራሳችንን ለመፈተሽ ወደ ዝሙት ከማምራት በሠራነው ሥራ መልካምነት ሙሉ እምነት ኖሮን ድንግልናችንን መጠበቅ ይገባናል::

በዝሙት መሸነፍ የሚጀምረው ድንግልናን መጠበቅ የማይቻል ነገር እንደሆነ ከማሰብ ነው:: አልችልም ያለ ተሸንፏልና:: ነገር ግን ለሚያምን እንኳን ድንግልናን መጠበቅ ይቅርና ከዚያም በላይ የሆነ ነገር ይቻላል:: «በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱም ደግሞ ያደርጋል:: ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል::» በማለት የሁሉ ፈጣሪ ለሰው ልጆች የገባው ቃል ኪዳን የሚሻር አይደለምና:: ዮሐ14፥12

ሰው ድንግልናውን ለመጠበቅ ዝንባሌ ሲኖረው መንፈስ ቅዱስ ይደግፈዋል:: ስለዚህ ራሱን ለመግዛትና ስሜቱን አሸንፎ ለመኖር ይችላል:: ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችም አንዱ «ራስን መግዛት» ነውና ገላ5፥23 ስለዚህ ንጽሕናውን ለመጠበቅ የኃይሉ ምንጭ መንፈስ ቅዱስ ከሆነ ድንግልናን ጠብቆ መኖር አይቻልም ለማለት አያስደፍርም:: ሐዋርያው «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» በማለት የተናገረው ቃል ድንግልናን ጠብቆ መኖርንም ይመለከታል:: ፊል4፥13 ስለዚህ በእምነት እየታገዙ ድንግልናን ጠብቆ መኖር ይቻላል:: ማቴ17፥20

በቅዱስ መጽሐፍ «ለሚያምን ሁሉ ይቻላል» እንደ ተባለው እንኳን ድንግልናን መጠበቅ ይቅርና ለማያምኑ ሰዎች የማይቻል የመሰለ ነገር ሁሉ ለሚያምኑ ሰዎች ይቻላል:: መንፈሳዊነት ማለት ረቂቅነት ማለት ነው:: ረቂቅነት ማለት ደግሞ ረቂቅ ነገሮችን ማሰብና ማድረግ መቻል ማለት ነው:: አንድ ክርስቲያን ድንግልናን መጠበቅ እንደማይቻል ነገር አድርጎ ካመነ መንፈሳዊ ነው ማለት እንዴት ይቻላል?

ድንግልናን መጠበቅ በኛ ዘመን የተጀመረ አዲስ ነገር አይደለም:: አዳም ከመሳሳቱ በፊት ለሰባት ዓመት ከሁለት ወር በገነት የኖረው ኑሮ ነው:: ኖኅም ለጋብቻና ለፍሬ የበቃው ለአምስት መቶ ዓመታት በድንግልና ከኖረ በኋላ ነው:: «ወዓቀበ ኖኅ ድንግልናሁ ሐምስተ ምዕተ ዓመተ ወነበረ እንዘ ይትለአክ ለሥጋ አቡነ አዳም በትእዛዘ እግዚአብሔር» ማለትም «ኖኅም በእግዚአብሔር ትእዛዝ የአባታችን የአዳምን ሥጋ እየጠበቀ ለአምስት መቶ ዓመታት ያህል በድንግልና ኖረ» ማለት ነው:: (ስንክሳር ጥር6)

## መታጨት፣ ማጨትና ማግባት በድንግልና ሊደረጉ ይገባል!

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሕግና ሥርዓት ማንኛውም ሰው ድንግልናውን ጠብቆ ማጨት፣ ካጨም በኋላ ድንግልናውን ጠብቆ እስከ ጋብቻው መቆየትና ማግባት ይኖርበታል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን በሙሽራ ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ በሙሽሪት መስሎ በተናገረበት አንቀጽ «እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ላንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና» በማለት በወርቁ የክርስቶስ ሙሽራ የምትባል ቤተ ክርስቲያን በቅድስና





የተዋበች መሆኗን አመልክቶ በሰው ደግሞ መተጫጨት መደረግ ያለበት ንጽሕናን ጠብቀው እየኖሩ በድንግልና መሆኑን ተናግሯል:: 2ቆሮ11፥2

ሊቀ ነቢያት ሙሴ በኦሪት «ማንኛውም ሰው ድንግልና ያላትን ልጃገረድ ቢያጭ» በማለት የተናገረው ቃል በድንግልና ሆኖ ማጨትና መታጨት እንደሚገባ ለማስረዳት ተጨማሪ መረጃ ይሆናል::

«ከተጫጨን ወዲህ መጋባታችን አይቀር ታዲያ የፈለግነውን ብናደርግ ምን አለበት?» በማለት ወደ ሩካቤ ማምራት አይቻልም:: ሳይጋቡ የሚደረግ ሩካቤ ነውረኛ ያሰኛልና:: 2ሳሙ13፥12-14 በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ የታጨችን ሴት «ልጃገረድ» እያለ ደጋግሞ መጥራቱ ያልተጋቡ ሰዎች ምንም ቢተጫጩ ሩካቤ መፈጸም የማይገባቸው መሆኑን ያስረዳል::

የተጫጩ ወንድና ሴት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጋብቻ ሳይፈጽምላቸው ካህኑ ፈቅደውልን ነው፣ ተማምለን ቃል ተገባብተናል፣ ልንጋባ የቀረን ጥቂት ቀን ወይም ትንሽ ነገር ብቻ ነው» የሚሉና ተቀባይነት የሌላቸው ሌሎችንም ምክንያቶች በመደርደር ሩካቤ ማድረግ አይገባቸውም:: የማይገባቸውም ሳይጋቡ ሊቀሩ ይችላሉ ከሚል ስጋት ብቻ ሳይሆን ቢጋቡም እንኳን ከመጋባታቸው በፊት በእጮኝነታቸው ወራት የፈጸሙት ሩካቤ ሕጋዊ ባለመሆኑ ዝሙት ሆኖ ስለሚቆጠር ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው አንድ እስራኤላዊ ሚስት አግብቶ ድንግልና ባያገኝባት ሚስቱን መክሰስ ይችል ነበር:: መንፈሳዊ ሕጉ እንደሚያዘውም በልዩ ልዩ መንገድ የሴቲቱ ክስ ይጠናና ክሷ ሐሰት ሆኖ ከተገኘ ከሳሽ ባሏ በእስራኤል ድንግል ላይ ክፉ ስም አምጥቷልና «መቶ የብር ሰቅል» ከተቀጣ በኋላ የከተማዋ

ሥጋን ከንጽሕና ተግባር ጋር አንድ አድርጎ መያዝ ይገባል:: 2ቆሮ11፥2 የቅድስና ሥራ የተለየው በአንጻሩ ደግሞ ርኩሰት የተዋሐደው ድንጋሌ ሥጋ አለ::በቅዳሜ ዕለት የሚነበብ የእመቤታችን ምስጋና «ተፈስሒ ኦ! ምልዕተ ጸጋ ድንግል ዘእንበለ ርኩስ» ይላል:: ትርጓሜውም «ያለ ርኩሰት ድንግል የሆንሽ ምልዕተ ክብር ሆይ ደስ ይበልሽ!» ማለት ነው:: (ውዳሴ ማርያም ዘቀዳም) ይልቁኑም «ያለ ርኩሰት ድንግል የሆንሽ» የሚለው ቃል ሰዎች በሥጋ ድንግል ሆነው ብዙ ርኩሰት ሊኖርባቸው እንደሚችል ሲያስረዳ የእመቤታችን ድንግልና ግን ፍጹምና ያለ ርኩሰት መሆኑን ያስገነዝበናል::

ደናግላን ቆነጃጅት ይባላሉ:: ቅዱስ ማቴዎስ የጠቀሳቸው አሥር ቆነጃጅት ደናግላን ናቸው:: አምስቱ ልባሞች ሲሆኑ አምስቱ ግን ሰነፎች ነበሩ:: ማቴ25፥13 እነዚህ ሰነፍ ደናግላን መብራታቸውን ይዘው ለመብራት የሚሆን ዘይት ግን አልያዙም ነበር:: ዘይቱን ሳይዙ መብራት መያዛቸው ብቻ ሙሽራው በመጣ ጊዜ አብረውት ወደ ሠርጉ ቤት ለመግባት አላበቃቸውም:: እንደዚሁ ሁሉ ንጽሐ ሥጋን ይዞ ንጽሐ ነፍስን ሳይዙ መገኘት ምንም አይጠቅምም:: ድንጋሌ ሥጋንም ያለንጽሕና ከብዙ ርኩሰት ጋር መያዝ ምንም እንደማይጠቅም በትርጓሜው ተብራርቷል:: ድንጋሌ ሥጋ እንደ መብራት ድንጋሌ ነፍስ ደግሞ እንደ ዘይት ነውና::

እንዲህ ከሆነ ከብዙ ነውረኛነት ጋር በሥጋ ብቻ ድንግል ብትሆን ምን ትጠቀማለህ? ምንም ሳይማሩ (ሳያውቁ) በመመረቂያ ልብስ (ጋዋን) ማሸብረቅና ምንም የንጽሕና ጉዳና ሳይከተሉ በሥጋ ብቻ ድንግል መሆን አንድ ናቸው:: ምነው ቢባል ቢያሳፍሩ እንጂ አያስከብሩምና:: ስለዚህ በፊቶች (ድንግልና በሌላቸው) ሰዎች ዘንድ





እንኳን የማይታይ የዝሙት ዓይነት እየፈራረቁ በሥጋ ብቻ ድንግል መሆን አያስመካምና ድንግልናን ከንጽሕና ጋር መጠበቅ ተገቢ ነው::

ድንግል ነኝን? ከሚለው ይልቅ ዋናው ጥያቄ መሆን ያለበት ድንግልናችንን እንድንጠራጠር ያደረገን ተግባር ኃጢአት ነውን? የሚለው ነው:: ማኅተመ ድንግልና ካልፈረሰ ኃጢአት (ዝሙት) አልተፈጸመም ማለት አይደለም:: ሰውን መግደል ዝሙት አይደለም ኃጢአትነቱ ግን እጅግ ታላቅ ነው:: «ወዘመዉ በጣዖቶሙ» ጣዖት ማምለክ ዝሙት ነው:: ድንጋሌ ሥጋን ግን አያጠፋም:: ግብረ ሰዶምም ማኅተመ ድንግልናን ላያጠፋ ይችል ይሆናል ዝሙት መሆኑን ግን ማንም አይክድም:: ስለዚህ የማይጠቅም ጥያቄ በማንሣት ጉልጭ አልፋ ክርክር ከመከራከር ኃጢያትን ማቆም ብልህነት ነው::

ድንግል ነኝን? የሚለው ጥያቄ ብዙ ጊዜ የሚፈጠረው ሰይጣን ሲተናኮል ነው:: ምክንያቱም ሁለት ልብ ያለው መወሰን ስለማይችል በመዘከን መሥራት ያለብንን ሳንሠራ እንድንቀር ዳግመኛም ደናግል እንደሆንን ቢነገረን ከባድ ኃጢአት እንዳልሠራን ቆጥረን እንድንጽናናና እንድንዘናጋ ለመድረግ ሲሆን በመጨረሻም ድንግል እንደማንባል ቢነገረን ደግሞ ከአሁን በኋላ ለምኔ እጠነቀቃለው? በማለኘት ተስፋ እንድንቆርጥ አድርጎ ወደ ዝሙት እንድንሄድ ለመገፋፋት ነው:: ስለዚህ ይህን ምሕዋረ ሰይጣን ተገንዝቦ ካለፈ መጥፎ ተግባር መሸሽ ብቻ የሚበጅ ይሆናል::

ከዚህም በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት ጥያቄ የሚፈጠረው ፍቅረ እግዚአብሔር ሲጉድልብንና ራስ ወዳድ ስንሆን ነው:: ምክንያቱም ግብረ ሰዶምን የመሰለ ብዙ ግብረ ዝሙት እየፈጸምን ያሳሰበን በደልነቱ ሳይሆን የድንግልናችን መጥፋትና

አለመጥፋት በመሆኑ ነው:: እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ «የቤተ ፊት» አስተሳሰብ ይባላል::

«ቤተ ፊት» የምትባለው ባል አግብታ እየኖረች ከጊዜ በኋላ ባሏን ፈትታ የኮበለለች ሴት ናት:: ከሄደችበትም ችግር ሲያጋጥማት የሚታያት ባሏን መበደሏ ሳይሆን ከባሏ ጋር በመትኖርበት ጊዜ የነበራት ምቾትና ክብር ነው::

አባታችን አዳምን ግን የቤተ ፊት ልማድ አላገኘውም:: ማለትም ኃጢአት ሠርቶ ከገነት በተባረረ ጊዜ ፈጣሪዬን አስቀየምኩት እያለ ስለ በደሉ ያለቅስ ነበር እንጂ የገነት ተድላ ደስታ ቀረብኝ እያለ ስላጣው ነገር አያዝንም ነበር:: «አልቦቱ ካልዕ ሕሊና ለአዳም ዘእንበለ ብካይ ላዕለ ኃጢአቱ - ስለ ኃጢአቱ ከማልቀስ በቀር ለአዳም ሌላ ሐሳብ አልነበረወም» የተባለው ስለዚህ ነው:: (መቅድመ ወንጌል)

እንደዚሁም ሁሉ ሰው በልዩ ልዩ ኃጢአት በተሰነካከለ ጊዜ «ድንግል ነኝን?» እያለ ያጣውንና ያገኘውን እያሰበ ከመተከዝ «አንተን ብቻ በደልሁ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ» በማለት ኃጢአቱን እያሰበ ቢያለቅስ በንስሐ አዳምን መስሎታልና የቤተ ፊት ልማድ አላገኘውም ይባላል:: መዝ50 ፥4

በመጨረሻም ድንግል ነኝ? የጋብቻዬስ አፈጻጸም ምን ይመስላል? ማለትም በተክሊል ማግባት እችላለሁ? ወይስ አልችልም? እያሉ በማሰላሰል ከመጨነቅ ባለፈው ክፉ ሥራ በመጸጸት ለወደፊቱ ደግሞ በመጠንቀቅና በመጠበቅ ከመምህረ ንስሐ ጋርም ውይይት በማድረግ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን በመመራት ልቡናን በአንድ ሐሳብ ማጽናት ይገባል::





## ድንግልናን መሳል ኃጢአት ነው?

በድንግልና ለመኖር መሳል ኃጢአት አይደለም:: ሆኖም ግን ፈታኝና አስቸጋሪ ነገር በመሆኑ በፍጥነትና በችኮላ መደረግ የለበትም:: ስለዚህ ነገር ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲህ ብሏል:: «እግዚአብሔር በሰማይ አንተም በምድር ነህና በአፍህ አትፍጠን:: በእግዚአብሔርም ፊት ቃልን ይናገር ዘንድ ልብህ አይቸኩል:: ስለዚህም ቃልህ ጥቂት ይሁን::» መክ5፥2 ስእለት አለመሳል መብት ሲሆን የተሳሉትን መፈጸም ግን ግዴታ ነው:: ስለዚህ «ተስለህ የማትፈጽም ከምትሆን ባትሳል ይሻላል» መክ5፥5 የተሳሉትን አለመፈጸም ኃጢአት ነውና::

በድንግልና ለመኖር መሳል ምን ያህል አስቸጋሪ መሆኑን አንጋፋ ደራሲ የተባሉት ሐዲስ ዓለምአየሁ «ፍቅር እስከ መቃብር» በተሰኘ መጽሐፋቸው «በዛብህ» በተባለው ገጸ ባሕርይ ላይ እንዲታይ አድርገዋል:: ስለዚህ በተለይ ወላጆች እነርሱ የማይኖሩትንና የማይቻላቸውን ኑሮ በልጆች ላይ መጫንና ልጆቻቸውን በድንግልና ኖረው ዘመናቸውን እንዲፈጽሙ ማስገደድ የለባቸውም:: እስከ ጋብቻ ድረስ በድንግልና እንዲቆዩ ለማድረግ ግን ከመምከርና ከማስተማር አንሥቶ ተገቢ የሆነውን እርምጃ ሁሉ የመውሰድ ኃላፊነት አለባቸው::

ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስንመጣ ደግሞ አንዲት ሴት በድንግልና ለመኖር ብትሳል ወላጆቿም ሆኑ ባሏ ሰምተው ከተቃወሙ ስእለቷ ሊፈርስባት ይችል ነበር:: በሰሙበት ዕለት ካልተቃወሟት ግን ስእለቷ ይጸና ነበር:: (ዘኁ30፥1-16)

ወደ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ደግሞ አንድ ሰው ድንግልናውን ጠብቆ ለመኖር ከተሳለ በኋላ እንደ ገና ወደ ማግባት ቢመለስ ጋብቻው ለሁለተኛ ጊዜ እንደሚያገባ ሰው ተቆጥሮ ሥርዓተ ተክሊል አይፈጸምለትም። (ፍት.ነገ.አን.24) ስለዚህ ድንግልናን ተስሎ ኋላ ከመቸገር ሳይሳሉ በልብ ንጽሕናን ለመጠበቅ መወሰንና ሲያቅት ወደ ጋብቻ መሄድ ይሻላል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ድንግልናውን በልቡ ይጠብቅ ዘንድ ቢጸና» በማለት እንደ ተናገረው ድንግልና የሚጠበቀው በልብ እንጂ በአፍ አይደለምና። (1ቆሮ7፡37)

## «ድንግል ነኝ!» ብዬ እጮኛዬን ዋሽሁት!

## ምን ይሻለኛል?

ምንም ዓይነት ሩካቤ ሳይፈጸም ድንግልና ሊወገድ የሚችልባቸው ብዙ ሁኔታች ተዘርዝረዋል። አንዳንድ ደካማ ሴቶች ድንግልናቸውን አስመልክቶ ለሚጠየቁት ጥያቄ ያሳለፉት ማንነታቸው ትችት ውስጥ ሳይገባ መልስ ለመስጠት በቂ ምክንያት ያገኙ እየመሰላቸው በዚህ ምክንያት ተሰነካክለዋል። ማለትም ድንግል ሳይሆኑ «ድንግል ነኝ» ይላሉ። ድንግል አለመሆናቸው የሚገለጥበት ጊዜ ሲመጣ ማለትም ሊያገቡ ሲሉ ደግሞ «ዝሙት ፈጽሜ አላውቅም ነገር ግን ድንግልናዬ በምን ምክንያት እንደ ጠፋ አልገባኝም!» በማለት ደረቅ ውሸት የሚዋሹ ብዙዎች ናቸው።

ሌሎች ሴቶች ደግሞ እውነቱ በሚገለጥበት ጊዜ «በዚህ ምክንያት ይሆናል እንጂ እኔ ዝሙት ፈጽሜ አላውቅም!» ብዬ ምክንያት እሰጣለሁ በሚል እሳቤ ድንግል አለመሆናቸው እያወቁ ወደ ፊት የሚያገቡትን ሰው «ድንግል ነኝ» እያሉ መዋሸታቸው ብዙ መዘዝ ሲያመጣባቸው ይታያል።





ግመል ቢሰርቅ በዚያ ቁመቱ ጉንበስ ብሎና ተደብቆ ማምለጥ አለመቻሉን ለመግለጽ «ግመል ሰርቆ አጐንበሶ» እየተባለ ይተረታል። በአንድ ወቅት በግድ ይፋ የሚሆን ነገርን ለመደበቅ መጣር ሞኝነት ነው። ታዲያ አንዳንድ ሴቶች ድንግልናቸውን በተመለከተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፈጦ የሚታየውን እውነት መደበቃቸው ምን ይባላል? ውሸት በምንም መልኩ መልካም ባይሆንም የዚህ ዓይነት ውሸት ግን ጨርሶ መሞከር የሌለበትና ከሁሉ የሚከፋ ነው። «እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር» እንደሚባለው እውነቱን ተናግሮ ከዚያ ተያይዞ የሚመጣውን ክፋም ሆነ መልካም ነገር መቀበል የተሻለ አማራጭ ነው። ይህ ሲባል ግን ባል ሚስትን ሚስት ደግሞ ባልን ይህን በመሰለ ነገር መደባበቅና መወሻሸት እንደሌለባቸው ለመናገር ነው እንጂ ለማንኛውም ሰው ይህን እውነት ወይም የግል ሕይወት መናገር አለብን ለማለት አይደለም። ሰው ሁሉ ይህን የግል ኑሮአችንን የማወቅ መብት የለውምና።

ድንግልና ከሩካቤ ውጭ በተለያየ መንገድ ሊጠፋ መቻሉን ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ወንዶችም የሚያውቁት ጉዳይ ነው። ነገር ግን ወንዶች ይህን ብቻ ሳይሆን ይህ ዓይነት ሁኔታ ሊፈጠር የሚችልበት አጋጣሚ በጣም ጠባብ መሆኑንም ያውቃሉ። ስለዚህ ብዙ ወንዶች በምንም ተአምር ሚስቴ ከወንድ ጋር ግንኙነት ሳይኖራት ድንግልናዋን በሌላ መንገድ አጣች ብለው ለማመን ይቸገራሉና። ይህን ማወቅ ዕወቀት ብቻ ከመሆን አልፎ የሚሰጣቸው ጥቅም አይኖርም።

በዚህ ምክንያት ምንም እንኳን ልዩ ልዩ ምክንያቶች ይዘውት ሐሳብሽን የተቀበለ ቢመስልም በልቡናው የሚኖረውን ጥርጥር ይህን በመሰለ ምክንያትሽ ከነ ስንኩፉ ማውጣት አይቻልሽም። ታዲያ በትዳር

ከሚጠብቁባቸው ምክንያቶች መካከል ጥቂቶቹን ለመግለጽ ያህል ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

ሀ. እንደ ብሔረሰቡ ልማድና ባሕል ይለያያል እንጂ ርእሰ ብሔር (ንጉሥ ወይም ንግሥት) ለመሆን ድንግል ሆኖ መኖር ግዴታ የሚሆንበት ብሔረሰብ አለ። በዚህ ዓይነት መንገድ ደናግላን ሆነው የሚኖሩ ሰዎች «ፓላስ ቨርጅንስ» ይባላሉ። ከዚህም አልፎ የቤተ መንግሥት ጠባቂዎችና ሠራተኞች የነገሥታት ሴቶች ልጆችን እንዳያባልጉ ሲባል ሕጽዋን (ጃንደረባ) ይደረጉ ነበር። ይህም ከቤተ መንግሥት እንብላ እንጠጣ በማለት ከሴት ሳይደርሱ ለመኖር ይህን ዓይነት ውሳኔ የሚወስኑ ሰዎች መኖራቸውን ያሳያል። ማቴ19÷12 ትርጓሜ

ለ. በድሮ ጊዜ ብዙ የፍልስፍና ሰዎች ሩካቤ ጥበብን ይሠውራል (ዕውቀትን አይገልጽልንም) ብለው ያምኑ ነበር። ስለዚህ በተቻላቸው ሁሉ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለመኖር የወሰኑ ብዙዎች ነበሩ። ይህን የሚያስረዳ ታሪክ በፊልክስዩስ መጽሐፍ ይገኛል። ፈላስፎች ባሕታውያንን ሊፈትኗቸው ሄዱ« እናንተ ትጾማላችሁ እኛም እንጾማለን። እናንተ ድንግልናችሁን እንደምትጠብቁት እኛም እንጠብቃለን ታዲያ እናንተ ከእኛ የምትበልጡት በምንድር ነው?» አሏቸው። ከባሕታዊያኑ መካከል አንዱ አረጋዊ ሲመልስ እንዲህ አለ፡- «ንሕነሰ ነዓቅብ አልባቢነ» ማለትም «እኛ ከእናንተ የምንለየውና የምንበልጣችሁ ልባችንን ስለምንጠብቅ ነው» አላቸው። ዛሬም ቢሆን በልዩ መንፈሳዊ ያልሆነ አመለካከት፣ ከፍርሐት፣ በብዙ ሥራ ከመጠመድ የተነሣ በድንግልና የሚኖሩ አንዳንዶች አሉ። የመንፈሳዊያን ሰዎች ድንግልና አጠባበቅ ግን ከእነዚህ ዓይነት ሰዎች ድንግልና አጠባበቅ በዓላማም ሆነ በይዘት በእጅጉ ይለያል። (ፊልክ. ክፍ.6 ተስ.78)





ሐ. ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ድንግልናቸውን የሚጠብቁ ሰዎች በእርግጥ ድንግልናቸው ምን ያህል እውነት ይሆናል? የሚለው ጥያቄ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ሰይጣንም ራሱ ደግሞ በግልጽ በድንግልና ሆናችሁ አገልግሉኝ የሚልበት ጊዜ ብዙ ነው። በዚህ መልኩ ለጣዖት አምልኮ የተለዩ ደናግላን «ፔስት ቨርጅንስ» ይባላሉ።

ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ድንግልናን መጠበቅ ለሰዎቹ ምንም እንኳን እንደ ሐሳባቸው የፈለጉትን ያገኙ ቢመስላቸውም ድንግልናን መጠበቅ ከሚያስፈልግበት ትክክለኛ መንገድ በተቃራኒው መንገድ በመፈጸሙ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከፍተኛ ወቀሳና ቅጣት ያስከትላል። ምክንያቱም ይህን ፈታኝ ጉዳይ ሰይጣንን ደስ ለማሰኘት ብሎ ለመፈጸም መቻል በከፍተኛ ሁኔታ ለሰይጣን መገዛትን ስለሚያመለክት ነው።

መ. ዛሬ ዛሬ ደግሞ ሁሉም ነገር ወደ ገንዘብ እየተመነዘረ በመምጣቱ ድንግልናን ለረጅም ዓመታት በመጠበቅ ነጥብ ወይም «ሪከርድ» ለማስመዝገብ ውድድር ውስጥ መግባት ተጀምሯል። ይህን ለመሰለ ጉዞም ራሳቸውን የሚያዘጋጁ አያሌ ሴቶች አይጠፉም።

ሠ. ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውጭ በመንፈሳዊ ጉዳና በባል ዘንድ ተወዳጅ ለመሆንና ላለመነቀፍ ሲሉ ድንግልናቸውን የሚጠብቁ ብዙ ሴቶች አሉ። ሌሎች ደግሞ ደናግል ባይሆኑ የሚቀርባቸው ክብረ ተክሊልና መንፈሳዊ የሠርግ ሥርዓት እየታያቸው ድንግልናቸውን ይጠብቃሉ። በእነዚህ ምክንያቶች ድንግልናን መጠበቅ የሚያስነቅፍ አይደለም። ምክንያቱም እነዚህ ድንግልናን ከምንጠብቅባቸው መንፈሳዊ ምክንያቶች ውስጥ በንዑስ ምክንያትነት የሚጠቀሱ በመሆናቸው ነው።

ሀ) የመጀመሪያው በድንግልና የመኖር ጥቅም «በአግባብ መኖር» ነው:: «በአግባብ መኖር» ሕግና ሥርዓትን እየፈጸሙ በአግባቡና በሥነ ሥርዓት መኖር ማለት ነው:: በድንግልና መኖር አግባብ ነው:: ዝሙት ግን ግብረ ገብነትን ማጣት ነው:: ድንግልናን ጠብቆ ለመኖር የሚደረገው ትግል ሕጋዊ ሰው ሆኖ መኖርን ያለማምዳል:: ታዲያ ድንግልናን መጠበቅ እንደ አሸዋ ሸክም ከከበደውና ንጽሕናን ከናቀ ከዚህ አመንዝራ ትውልድ ግብረ ገብነትን መጠበቅ ከዝንብ ማር እንደ መጠበቅ አይሆንምን?

ለ) ሁለተኛው በድንግልና የመኖር ጥቅም «ሳይባክኑ» መኖር ነው:: በድንግልና የሚኖር ሰው አይባክንም ወዲህና ወዲያ አይልም:: ዝሙት ግን መባከን ነው:: ለምን ቢባል ዝሙተኛ ኃጢአቱን ለመደበቅ፣ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ምን ያመጣብኝ ይሆን? በማለትና ዝሙቱ ቢታወቅ በሌሎች ዘንድ ምን ሊባል እንደሚችል በማሰብ በስጋትና በመባከን ይኖራል:: ዝሙት ያባክናልና:: በተጨማሪም ዛሬ ዛሬ በዝሙት ጠንቅ በሚመጣ በሽታ ተይዤ ይሆን? ከማለት የሚበልጥ መባከን ምን አለ?

ቅዱስ ዳዊት «ወተአውከት እምመዓት ዓይንየ» በማለት ተናግሯል:: እንዲህም ማለቱ «ሴቶችና ሕፃናት ሲቆጧቸው ከአሁን አሁን ዱላ ጣሉብን በማለት ዓይናቸው እንደሚባክነው እኔም ጉልማሳ ገድዬ በጎልማሳ ሚስት በማመንዘሬ ምን ትቀጣኝ ይሆን? በማለት ባከንኩኝ» ለማለት ነው:: መዝ6፥1-3 ስለዚህ ዝሙት በዚህ ብቻ ሳይሆን በሌላም በብዙ መንገድ ሰውን ሲያባክነው ይታያል:: ድንግልናን ለመጠበቅ የሚጣጣር ሰው ግን ዝሙት ከሚያመጣው መባከን ፈጽሞ የዳነ ነው:: መዝ6፥2-3





ሐዋርያው ሰዎች በድንግልና እንዲኖሩ የሚያበረታታበትን ምክንያት ሲገልጽ «ያለ ሐሳብ ልትኖሩ እወዳለው» ብሏል:: 1ቆሮ7፥32 ምክንያቱም ያገባ «የዓለምን ነገር ያስባልና፣" ልቡም ተከፍሏል» ይላል:: 1ቆሮ7፥33 በዝሙት ከመኖር በጋብቻ መኖር ሐሳብ ያቀላል:: በጋብቻ ከመኖር ደግሞ በድንግልና መኖር የበለጠ ከሐሳብ ነጻ ያደርጋል:: ስለዚህ ሐዋርያው «ያለ ሐሳብ ልትኖሩ እወዳለው» በማለት መክሯል:: ከዚህ የሐዋርያው ቃል በመነሣት «ሳይባክኑ መኖር» ድንግልናን ከመጠበቅ የሚገኝ ዋነኛ ጥቅም መሆኑን መረዳት ይቻላል::

ሐ) ሐዋርያው በጥቂት ገጽ ንባብ ካሰፈራቸው ድንግልናን የመጠበቅ ጥቅሞች ውስጥ ሦስተኛውና የመጨረሻው «በጌታ እንድትጸኑ» የሚለው ነው:: ድንግልናን መጠበቅ በጌታ ያጸናል:: ይህም ማለት ስለ ፍትወት ብለው ኮረዳና ጎልማሳ ፍለጋ ብዙዎች ሃይማኖታቸውን እንደተዉ የሚታወቅ ነው:: «በመዳራታቸውም ብዙዎች ይከተሏቸዋል» እንደተባለው ብዙዎች በዝሙት ማዕበል እየተገፉ ከሃይማኖት ወጥተዋል:: ድንግልናውን ለመጠበቅ የቆረጠ ሰው ግን የሃይማኖት ሙቀቱ ሳይበርድበት ለፈጣሪው ባለው ፍቅር ጸንቶ ይኖራል:: 2ጴጥ2፥1-2

ይህም ብቻ ሳይሆን ድንግልናን መጠበቅ ራሱ ጽናትንና ትዕግሥትን ይጠይቃልና ስለዚህ «በጌታ እንድትጸኑ» አለ:: በተጨማሪም «ድንግልናውን በልቡ ይጠብቅ ዘንድ ቢጸና» 1ቆሮ7፥37 በማለት ሐዋርያው የተናገረው ቃል «ጽናት» ከድንግልና ጋር ያለውን ትሥሥር ያሳያል:: ድንግልናን በመጠበቅ ጽናትንና ትዕግሥትን የመሳሰሉ መንፈሳዊ ተግባራትን እንማርበታለን:: ስለዚህ ድንግልናውን ለመጠበቅ የቆረጠ ሰው በዓላማው ሁሉ ትዕግሥተኛና

ጽኑ ሰው መሆኑን መናገር ይቻላል:: ታዲያ ይህን የመሰለ ጥቅም ማግኘትን የሚያህል ምን ነገር አለ? አንተ ሰው ጽኑ ነህን? ለማለት ድንግልናህን ጠብቀህ እስከ አሁን አለህን? ቢባል ስንቶቻችን ፅናት እንደሌለን ይረጋገጥ ይሆን?

መ) ድንግልናን ጠብቆ መኖር ታማኝነትን ያረጋግጣል:: ምክንያቱም ድንግልና በሥርዓት ጠብቀን እንድንይዘው በአደራ እንደ ተሰጠን የከበረ ንብረት ነውና:: ባለ አደራው ፈጣሪያችን በሚያስፈልግ ጊዜና ሰዓት ለትዳር አጋራችን እንድንሰጠው ይጠብቅብናል:: በዚህ ጊዜ ድንግልናው ጠብቆ እስከ ጋብቻ ጊዜው ድረስ ያልቆየ ሰው አደራ በሊታ ይባላል:: ታማኝነትም የጕደለው ይሆናል:: ሰው ደግሞ በዚህ ካልታመነ በሌላ ነገር በምን ሊታመን ይችላል?

ድንግልናን መጠበቅ «በባልና በሚስት መካከል መተማመንን» ይፈጥራል የሚባለው የታማኝነት ምልክት ስለሆነ ነው:: ባል ሚስቱን በምን ይመን? ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ያልታመነች በሰው ዘንድ ታማኝ ልትሆን እንዴት ትችላለች? ስለዚህ ድንግልናን ጠብቆ በመኖር ታማኝነትን ማስመስከር ይገባል:: ማኅተመ ድንግልና የታማኝነት ማረጋገጫ ምስክር ነውና::

ድንግልና በሩካቤ ሥጋ ይጠፋል:: ይህ ተግባር ደግሞ በዓይን እንደ መጥቀስና እንደ ማስነጠስ በቅጽበትና ሳይታሰብ የሚከናወን ተግባር አይደለም:: ሩካቤን ለመፈጸም የሚያስችል ምቹ ቦታ ለማሰናዳት ከሚደረግ ጥረት እንሥቶ ብዙ ሂደቶችን በማለፍ የሚከናወን በመሆኑ በእጅ እንደያዙት ብርጭቆ ድንገት ሳላስበው ወድቆ ተሰበረብኝ የሚባል ነገር አይደለም:: በመሆኑ ድንግልናን ያለ ጊዜው ማጥፋት ታማኝነትን እንደ ማጣት እንጂ እንደ አንድ ተራ ቅጽበታዊ ስሕተት ለመቁጠር ያስቸግራል::





በሩካቤ ጊዜ ባል ለሚስቱ ድንግልናውን ያስረክባል:: ምንም እንኳን በግዘፍ ልዩ ምልክት ባይኖረውም ረቂቅ የፍቅር ቋንቋ አለውና ይገባቡበታል:: ሚስት ደግሞ በረቂቅም በግዘፍም ድንግልናዋን በክብረ ስጦታነት ለባሏ ታበረክታለች:: በዚህ ጊዜ ለባሏ እንድትሰጥ እግዚአብሔር በሚስቱ ያቆየለትን አደራ ባል ሲቀበል (ድንግልናዋን ሲያገኝ) ሚስቱን በአደራ ጠባቂነት እንዲያያት፣ እንዲያምናት፣ እንዲያከብራትና እንዲወዳት ያደርገዋል:: ባልና ሚስት እንዲፈቃቀሩ፣ እንዲተማመኑና እንዲከባበሩ ድንግልናን ጠብቆ መገኘት ወሳኝ የሚሆነው ስለዚህ ነው::

ድንግልናን መጠበቅ ችሎታ ነው:: ምክንያቱም በውስጡ ጽናት፣ ብርታት፣ ትዕግሥት፣ ታማኝነት አለበትና:: ድንግልናን መጠበቅ ፍቅር፣ ባልን ማክበር፣ ራስን ማክበርና የመሳሰሉት በውስጡ ይገኙበታል::

ሠ) ድንግልናን መጠበቅ መጠንቀቅ ነው:: እንዲያውም መጠንቀቅ ተብለው ከሚወሰዱ ማንኛውም ዓይነት ሌሎች እርምጃች ምንም ዓይነት ሰብአዊ ቀውስ ሳያስከትል መከናወን የሚችል ተገቢ የጥንቃቄ ዓይነት ነው:: ከበሽታ፣ ያለ አግባብ ወይም ሳያገቡ ከመውለድ፣ ክብርንና መልካም ስምን ከማጣት፣ ከመጸጸት በአጠቃላይ ለወደፊት መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ችግር ከሚፈጥሩ የኑሮ ጠንቆች ሁሉ መቶ በመቶ ሊሰውር የሚችል መጠንቀቅ ቢኖር ድንግልናን መጠበቅ ነው::

ረ) አንዲት ሴት በድንግልና ኖራ ብታገባ ልቧ አይከፈልምና ፈጣሪዋን እጅግ አድርጋ ታስደስተዋለች:: ሐዋርያው «ያልተጋባች ሴትና ድንግል በሥጋም በነፍስም እንዲቀደሱ የጌታን ነገር ያስባሉ» ያለው ስለዚህ ነው:: ድንግል ሴት በድንግልና ኖራ ስታገባ ደግሞ

ባሏን በጣም ታስደስተዋለች:: ማንኛውም ባል ሚስቱን ድንግል ሆና ቢያገኛት ይደሰትባልና:: ድንግል ባትሆን ግን ባልዋን እንዴት ልታስደስተው ትችላለች? በእርግጥ ባልን ማስደሰት የሚቻለው በዚህ ብቻ ባይሆንም የሚጀምረው ግን ከዚህ ነው::

ድንግልናን ካጠፉ በኋላ የሚደረግ ጋብቻ አግብቶ የፈታ ሰው እንደሚፈጽመው እንደ ሁለተኛ ጋብቻ ይቆጠራል:: ምክንያቱም የተጋቡ ሰዎች ብቻ ሊፈጽሙት የሚገባውን ሩካቤ ሥጋ ከጋብቻ በፊት ፈጽሞ በመገኘቱ ነው:: ለመመንኮስ ተስሎ የነበረ ሰው ቢያገባ የተሳለው ስእለት እንደ መጀመሪያ ጋብቻ ተቆጥሮ የሚፈጽመው ጋብቻ ለሁለተኛ ጊዜ እንደሚያገባ ሰው እንደሚቆጠርበት ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ ይናገራል::

ይህ እንዲህ ከሆነ ድንግልናቸውን ያጡ ሰዎች የሚፈጽሙት ጋብቻ እንደ መዓስባን ወይም እንደ ሁለተኛ ጋብቻ መቆጠሩ ምንም አያስደንቅም:: እዚህ ላይ በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ለሁለተኛ ጊዜ የሚያገባ ሰው ማለትም ሚስቱ ሞታበት ወይም ለፍቺ በሚያበቃ ምክንያት ተለያይተው ከሆነ ፈቅዶ እንዳደረገው እንደ መጀመሪያ ጊዜ ጋብቻው ደስተኛ እንደማይሆን ነው:: እንደዚሁም ሁሉ ፈት ሆኖ ማግባት ድንግል ሆኖ እንደ ማግባት አያስደስትም ወይም ፈትን ማግባት ድንግልን እንደ ማግባት አያስደስትም::

ከዚህም በተጨማሪ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንደሚያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል፡ ልቡም ተከፍሏል::» ስለሴቶች ደግሞ «የተጋባች ግን ባሏን እንዴት ደስ እንደምታሰኘው የዓለም ነገር ታስባለች::» 1ቆሮ7፥33-34 ብሎ በተናገረው መሠረት ያገቡ ሰዎች ልቡናቸው እንደሚከፈልና እግዚአብሔርን በአንድ ልብ ሆነው ለማምለክ እንደሚቸገሩ ሁሉ





ድንግልናቸውን ካጡ በኋላ ያገቡ ሰዎችም እንደዚሁ ልቡናን የሚከፍል ተግባር የፈጸሙ በመሆኑ በሙሉ ልብ አንዳቸው አንዳቸውን ማስደሰት ይሳናቸዋል::

እንደዚህ ያሉ ባለትዳሮች ሩካቤ በሚፈጽሙበት ጊዜ ከዚያ አስቀድሞ ድንግልናቸውን ያጡበትን መንገድ ክፉም ሆነ ደግ መስሎ በታያቸው መልኩ በሕሊናቸው ማሰላሰላቸው የማይቀር ነገር ነው:: ይህ ዓይነቱ የሐሳብ መከፈል ደግሞ እየፈጸሙት ባለው ሕጋዊ ሩካቤ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያመጣል:: ስለዚህ ባል ሚስትን ሚስት ደግሞ ባሏን በሙሉ ልብ ማስደሰት አይችሉም መባሉ ትክክል ነው:: ይህ የልቡና መከፈል የሚፈጠረው ድንግልናውን ባልጠበቀው ወገን ብቻ ላይሆን ይችላል:: ድንግልናውን ጠብቆ የኖረውም ወገን ድንግልናውን ስላጣው (ስላጣችው) ወገን ሕይወት በሕሊናው መመራመር ይፈጠርበታል:: ስለዚህ ምንም በአካል መዋሐድ ቢችሉም የልቡና ተዋሕዶ ለመፍጠር ይቸገራሉና ደስታቸው በእጅጉ ይቀንሳል::

ይህን ለመሰለ ችግር መፍትሔው ከሁሉ አስቀድሞ ድንግልናን ማጣት የሚያስከትለውን አካላዊና ሕሊናዊ ቀውስ በመረዳት ድንግልናን መጠበቅ ሲሆን በተረፈ ግን በተቻለ መጠን ያለፈን ሕይወት አምኖ በመቀበል መርሳትና ለወደፊቱ የሚበጀውን ብቻ ማድረግ ይሆናል::

ሰ) ድንግልናን ጠብቆ መኖር ጋብቻ ሳይዘገይ በጊዜው እንዲፈጸም ይገፋፋል:: ምክንያቱም ማንኛውም ጤናማ ሰው የተቃራኒ ፆታ አቻውን የመሻት ዝንባሌ አለው:: ታዲያ ይህ በውስጡ የሚገኝ ሩካቤ መሻትና ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ሕገ ወጥ ሩካቤን ላለመፈጸም (ድንግልናውን ጠብቆ ለመኖር) የሚያደርገው ጥረት የሚታረቁለት ሲያገባ ብቻ በመሆኑ ድንግልናውን ጠብቆ እስከ ጋብቻ

ለመቆየት ዓላማ ያለው ሰው በውስጡ ያለውን የፍትወት ግፊት ለማብረድ ሲል ቶሎ ብሎ ማግባት እንዳለበት ይሰማዋል::

ድንግልናን ስለመጠበቅ ግድ የሌላቸውና ቀድመ ጋብቻ የሚደረግ ዝሙትን የተለማመዱ ሰዎች ግን ጋብቻን እንደ መታሰር ስለሚቆጥሩትና በውስጣቸው ያለውን የፍትወት ግፊት እንደ ፈቃዱ እያስተናገዱት በመሆኑ ወደ ጋብቻ የሚገፋቸው ውስጣዊ ኃይል ስለሚቀንስ ከማግባት ይቦዝናሉ:: ስለዚህ በዘማዊያን ዘንድ ዘግይቶ ማግባት የተለመደ ነው:: ድንግልናቸውን ጠብቀው የኖሩ ሰዎች ግን ወደ ጋብቻ ለማምራት ቆራጦች በመሆናቸው ውሳኔያቸው እጅግ ፈጣን ነው::

ጋብቻ ለመፈጸም የሩቅ ቀጠሮ ያላቸው ሰዎች እንኳን ከጋብቻ በፊት ምንም ዓይነት ሩካቤ ማድረግ እንደማይፈቀድላቸው ሲያውቁ የጋብቻ ቀጠሮአቸውን በማሳጠር የአግቡኝ ሮሮ የሚያሰሙት በዚህ ምክንያት ይመስላል::

ሸ) ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ሩካቤ ሥጋ የጋብቻን ቀነ ቀጠሮ እንዲራዘም ከማድረጉም በላይ ለመለያየትም በር ከፋች ነው:: የተጋቡ ሰዎች ሩካቤ ለመፈጸም የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ለመለያየት እንደሚገፋፉ ሁሉ ያልተጋቡም ሰዎች ሩካቤ መፈጸማቸው እንዲለያዩ ዓይነተኛ ምክንያት ይሆናል:: እንደ አምኖን የሚሹትን ሲያገኙ «ለዚህ ሴትነትሽ ነውን?» የሚሉ ወንዶች ቁጥር እጅግ በርካታ ነው:: 1ሳሙ 13፥14-16

ቀ) አስቀድሞ የምንኩስና ዝንባሌ ያለው ሰው ከጋብቻ በፊት ሩካቤ መፈጸሙ የበለጠ ወደ ምንኩስና እንዲገፋፋ ይሆናል:: ይህ አካሄድ ግን ለፈተና የሚመጣ እንጂ ለመልካም አይደለም:: በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚሆን ምንኩስና አይሆንምና:: እንዲህ





ዓይነት ሰው በመጀመሪያ የሥጋ ፈተና ጨርሶ የራቀለት ይመስለዋል:: በመቀጠልም ቢመነኩስ ሥርየት እንደሚያገኝ ይሰማዋል:: ከዚህ ይልቅ ግን የሌላውን ሕይወት አበላሽቶ መመንኩስ እንደማይገባው ቢሰማው የተሻለ ነበር:: ለራሱም ቢሆን ጣዕመ ዓለምን ባቀምስ መልካም ነበር:: ለምንኩስናውም ይረዳው ነበር:: ነገር ግን ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ሰይጣን በስሜት እየነዳ እንዲመነኩስ ያደርገዋል:: ስለዚህ ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ሩካቤ በምንም መልኩ ጠቃሚ አይደለም:: ለምንኩስና መገፋፋቱም አሉታዊ እንጂ አዎንታዊ ገፅታው አይደለም::

በአጠቃላይ ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ግንኙነትና ድንግልናን ማጣት በባልና በሚስት መካከል ደስታን፣ መተማመንን፣ ፍቅርን ይቀንሳል:: መጸጸትንና ሰላም ማጣትን በመካከላቸው ይፈጥራል:: ለልዩ ልዩ በሽታዎችና ላልታሰበበት እርግዝና ከዚያም አልፎ ለውርጃ ያጋልጣል:: ያለ ጋብቻ መዘግየትን ያመጣል:: አለመጽናትን፣ አለመታገሥን፣ አለመታመንንና የመሳሰሉትን ያመለክታል:: ብዙ መንፈሳዊ ጸጋዎችንም ያሳጣል:: ያለ አግባብ ለመመንኩስ ወይም ደግሞ ለባሰ የዝሙት ተግባር ሊገፋፋም ይችላል::

## ድንግልናን የሚያሳጡ አደገኛ ወቅቶች፣

## ቦታዎችና አጋጣሚዎች!

ሕጋዊ ባልሆነ ሩካቤ ምክንያት ሰዎች ድንግልናቸውን የሚያጡት በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ላይ እያሉ ነው:: አንዳንዶች ገና በልጅነትና በመጀመሪያዎቹ የወጣትነት አፍላ ጊዜያት ድንግልናቸውን ያጣሉ:: ሌሎች ደግሞ አስቸጋሪውን የወጣትነት ዕድሜ አጋምሰው ክብራቸውን የሚያጡበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ጥቂቶች ደግሞ ያን

ሁሉ የወጣትነት ፈተና ካገባደዱ በኋላ ወደ መጨረሻ ሲደርሱ ክብራቸውን የሚያጡበት ጊዜ አለ:: በዚህ መልኩ ከፍጻሜ ሲደርሱ ለክብር አለመብቃት በእጅጉ ያስቆጫል::

ይህ የሚሆነው ልጆች ስለተቃራኒ ፆታ ግንኙነት ከሚኖራቸው የአመለካከት ልዩነት፣ ለዚህ ዓይነቱ ግንኙነት ከሚኖራቸው መጋለጥ፣ ከራሳቸው መንፈሳዊና አካላዊ ጥንካሬ፣ ከባሕልና ከአስተዳደግ ልዩነት ወዘተ የተነሣ ነው:: ሆኖም ግን ብዙ ነገር ተቋቁመው ካለፉ በኋላ የፈተናው መጠን በሚቀንስበትና ወደ ጋብቻ በሚቃረቡበት ሰዓት ሳያገቡ ድንግልናን ማጣት ከሁሉ የበለጠ የሚያስቆጭ ነው::

ከሁሉ የሚያሳዝነው «ድንግልናዬን ያጣሁበትን መንገድ ምንም እንኳን በመንፈሳዊ ዓይን ሳየው ሥራዬ እጅግ ቢያስቆጨኝም በወቅቱ ግን ያን በማድረጌ ደስተኛ ነበርኩኝ» በማለት ለመናገር የሚደፍሩ ጥቂቶች ብቻ መሆናቸው ነው:: ምክንያቱም የብዙዎች ሰዎች ድንግልና ማጣት በአንድ ወገን ጫናና ፍላጎት ብቻ የተፈጸመ ከመሆኑም በላይ በቦታ ዐቅም እንኳን ጎንን ማሳረፊያ በሌለበት በየሜዳውና በየፈፋው፣ በአጥር ጥግና በመኪና ውስጥ፣ በፊልም ቤት፣ በምግብ ማብሰያና በመጸዳጃ ቤት፣ በየትምህርት ተቋማት ማደሪያዎች፣ በቢሮዎችና በየኮሪደሩ፣ በድብደባ፣ በጉተታና በልዩ ልዩ መንገድ የተፈጸሙ በመሆናቸው ነው:: ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በምንም ዓይነት ምቾት ቢሆን ድንግልናን ያህል ነገር ከጋብቻ ውጭ ማጣት የሚያሳዝን ነገር ቢሆንም በዚህ መልኩ መሆኑ ደግሞ ሲታሰብ እንኳን ይዘገንናል::

ከዚህ በታች ድንግልናን ለማጣት የሚዳርጉ ወሳኝ ወቅቶች፣ ቦታዎችና ሁኔታዎች ተዘርዝረዋል:: የተነሡት ነጥቦች አብዛኞቹ እውነተኛ ታሪኮች ናቸው:: ሆኖም «ታሪክ ራሱን ይደግማል»





እንደሚባለው እነዚህ ሰዎች በተጓዙበትና በተጎዱበት የስሕተት ጐዳና የሚሯሯጡ ብዙ ሰዎች ዛሬም ይገኛሉ:: ብልህ ሰው ከሰው ጉዳት ብዙ ይማራል:: በራስ ላይ ክፉ ነገር ሳይደርስ በሌሎች ከደረሰ ጉዳት መማር ታላቅ ዕድል ነው::

ሀ. ብዙዎች ክብረ ድንግልናቸውን ያጡበት መንገድ ተገድዶ መደፈር ነው:: ይህ ጉዳይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ዐቢይ መነጋገሪያ እየሆነ ከመጣ ዘመናትን አስቆጥሯል:: በመጽሐፍ ቅዱስም ስለ አስገድዶ መድፈር ተጽፏል:: በወቅቱ በደፋሪነት የሚታወቀው ወንድ ተደፋሪዋ ደግሞ ሴት በመሆኗ ደፋሪው ስለሚገባው ቅጣት ተደፋሪዋ ማድረግ ስላለባት ነገር በዝርዝር ተጽፎ ነበር:: ዘዳ22፥23-27

እንደ ሥርዓተ ኦሪት ከሆነ ተደፋሪዋ ሴት ድርጊቱን መቃወሟ የሚታወቀው ቢያንስ «መጮኽ» በሚቻላት ጊዜ ሁሉ «መጮኽ» ከቻለች ብቻ ነበር:: ይህ ካልሆነ ግን በድርጊቱ እንደተስማማች ይቆጠርና ከደፋሪዋ ጋር እርሷም አብራ በድንጋይ ትወገር ነበር:: ለምን ቢባል «በከተማ ውስጥ ሳለች አልጮኸችምና» በማለት ቅዱስ መጽሐፍ መልስ ይሰጠናል:: ዘዳ22፥24

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥርዓት የሚያስተምረው ከመደፈር ለመዳን ሴቶች ከ«መጮኽ» አንሥቶ በአለባበስ፣ በድርጊት፣ በቦታ፣ ወንዶች ሥጋ እንዳየ አንበሳ በኃይል እንዲነሡባቸው ከማድረግ በመቆጠብ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለባቸው ነው::

«መብቴ ነው» እያሉ እንደፈቀዱ መሆን ይቻል ይሆናል:: መብትሽ ከሰው በታች የሚያደርግሽ ከሆነ ምን ይረባሻል? በመንፈስ፣ በሥነ ልቦናና በአካል ጉዳት ላይ ከወደቅሽ በኋላ ለዚህ ያበቃሽ ሰው በሕግ መቀጣቱ ተገቢ ነገር ነው:: ቢሆንም ላንቺ ግን እንኳን መታሰሩ ብቻ ይቅርና በስቅላት የሚቀጣም ቢሆን ምንም አይጠቅምሽም:: ላንቺ

የሚበጅሽ ከመጀመሪያው ጉዳት ባይደርስብሽ ነውና:: ስለዚህ ከወዲሁ ራስሽን ለአስገድዶ መደፈር አታጋልጪው::

ለ. መደፈር በኃይል በመገደድ ብቻ አይደለም:: ከመነሻው ከወንዶች ጋር የሚኖርሽን ግንኙነት በጥንቃቄ አድርጊ:: እርዳታ ካስፈለገሽ አቋምሽን ገልጸሽ በቀና የመረዳዳት መንፈስ እርዳታ ተቀበይ:: አንቺም ሌሎችን ስትረጂ በዚሁ መንገድ አድርጊው:: በእርዳታና በውለታ ብዛት መደፈር አለና ያለ አግባብ እርዳታ ብታገኚ ሳትወጂ በግድ ራስሽን ትሰጪያለሽ:: ስለዚህ እርዳታ ከመጠየቅ ወይም ከመቀበልሽ በፊት በውኑ ይህን ዓይነት እርዳታ የሚያስፈልገኝ ሰው ነኝን? የሚረዳኝስ ሰው ምን ዓይነት ነው? ዖታው፣ እድሜው፣ የኑሮ ሁኔታው፣ ቅርርባችንስ ምን ያህል ነው? ወይም ምን ይመስላል? ለምን ይረዳኛል? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ አግኝ ላቸው:: ይህ ሰው ለኔ የሚያድርገውን ያህል እርዳታ የሚያስፈልጋቸውና ከኔ ይልቅ የሚቀርቡት ሌሎች ወገኖች የሉምን? ታዲያ እኔ በምን ምክንያት ቀዳሚያቸው ሆንኩኝ? በመጨረሻም ምን አልባት በመጨረሻ ከዚሁ ሰው ያላሰብኩት ዖታዊ ጥያቄ ቢሰነዘርብኝ በምን መልኩ መልስ መስጠት እችላለሁ? ብለሽ አስቢበት::

እግዚአብሔር ስለ ንጽሕና ከሰው የሚፈልገው ንጽሕናን ብቻ ነው:: ዝሙት በንስሓ እንጂ በምጽዋት ሊሠረይ አይችልም:: ንጽሕና በዋጋ የሚሸምቱት ሸቀጥ አይደለምና:: ምጽዋት ተቀባይነት የሚኖረው ከንጽሕና ሥራ ጋር ሲተባበር ነው:: እንዲህ ከሆነ በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን ለተዋለልን ውለታ በሰውነታችን ለመክፈል ማሰብ ሞኝነት ነው:: ውለታ ከተቻለ በዚያው መንገድ ሊከፈል ይገባል:: ካልሆነም «እግዚአብሔር ይስጥልኝ» ማለት ብቻ ውለታን ሊመልስ ይችላል:: ምክንያቱም ውለታ ብድር አይደለምና:: ሆኖም ይህ ምስጢር ሳይገባቸው ቀርቶ ለማግኘት ስለሚፈልጉት ነገር ወይም





አስቀድሞ ስለተደረገላቸው ውለታ ሰውነታቸውን ለዝሙት አሳልፈው የሚሰጡና ድንግልናቸውንም በዚህ መንገድ እያጡ ያሉ ሴቶች ቁጥር እጅግ ብዙ ነው:: አንቺስ በሕይወትሽ የምትመኚውን ትልቅ ነገር ሊያደርግልሽ የሚችል ወንድ ብታገኚ በድንግልናሽ እንደማትዋዋዪ ምን ያህል እርግጠኛ ነሽ?

ሐ. ከለላ ለማግኘት ስትዪ ከአንዱ ወንድ ጋር እጅግ አትጣበቂ:: ከፈራሻቸው ሌሎች ይልቅ መጥፊያሽ የተማመንሽበት እንዳይሆን ተጠንቀቂ:: እንዲህ ባለ ጉዳና ብዙዎች ተሰናክለዋልና:: እጅግም በሰው መተማመን አይገባም:: እርሱ ራሱ ሸክላ ነውና:: ለምሳሌ:- በሚያስፈራ ጭለማ ብትሄጂ በራስሽ መመዘኛ ከሰከረ ያልሰከረውን ከእብድ ይልቅ ደግሞ ያልቀወሰውን ተማምነሽ ትጠጊ ይሆናል:: እነዚህን ግን ማን የተሻሉ አረጋቸው? ብሰውስ ይገኙ እንደ ሆን ምን ታውቂያለሽ ? ስለዚህ ይህን በመሳሰለ ጥርጣሬ ብትሄጂ ሊያገኝሽ የሚችለው ጉዳት በእጅጉ ይቀንሳል:: ሰውን ማመን አያጸድቅምና::

መ. የሰው ባሕርይ እንደ ተቀጠቀጠ ሸንበቆ ነው:: ብዙ ሲደገፉት መሰበሩና መውጋቱ አይቀርም:: በራስም ሆነ በሌላ ሰው ብዙ መተማመን አይገባም:: ብዙ ጊዜ ስሜት ከዕውቀት ይልቅ ይበረታል:: መጥፎነቱን እያወቅን ማድረግ የማንፈልገውን ነገር ደጋግመን ለመሥራት የምንገደደው ስሜት ከዕውቀት ይልቅ ስለሚበረታ ነው::

ብዙ ሰዎች ድንግልናቸውን ሲጠብቁ ኖረው ከዚህ ክብር የሚወድቁት ጋብቻቸውን ለመፈጸም ጥቂት ቀናት ወይም ሰዓታት ሲቀራቸው ነው:: ይህም የሚሆነው ከላይ እንደተገለጸው ቀኑ በቀረበ ቁጥር የኀኀት ስሜት እየተሰማቸው በሚፈጥሩት መቀራረብና

መተማመን ምክንያት ስለሚዘናጉ ነው:: ስለዚህ ይህን አስቸጋሪ ወቅት እንደወትሮው ሁሉ መቀራረብን በልክ አድርጐ በጥንቃቄ መጓዝ ያስፈልጋል:: እንዲህ ካልሆነ የአንዲት ቅፅበትን ስህተት በዕድሜ ልክ እንባ ማጥራት ሊሳነን ይችላል::

ከላይ የተጠቀሰውን የማሳሳቻ ዘዴ (ማዘናጋት) በመጠቀም እንጋባ የሚል ሐሳብ ሲነሣ ጆሮአቸውን ይይዙ የነበሩ ወንዶች ከጋብቻ በፊት የሩካቤ ጥያቄ አንሥተው ውድቅ ሲሆንባቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማግባት እንደወሰኑ ቃል መግባትና መሐላ መደርደር ይጀምራሉ:: ይህን የሚያደርጉት «የሚያገባኝ ከሆነ ምን አስጨነቀኝ» በማለት አቋምሽ እንዲላላና እንድትዘናጊ ለማድረግ ነው:: ይህንን በመሰለ ጊዜ አለመፈታትና አቋምን ጥብቅ አድርጐ በመያዝ እስከ ጋብቻ ዕለት ድንግልናን ጠብቆ መቆየት አግባብ ነው::

ሠ. ስለወር አበባ በተጻፈበት አንቀጽ እንደተገለጸው በወቅቱ ልዩ ልዩ የሕመም ስሜት እንደሚኖር የታወቀ ነው:: በዚህ ጊዜ ሕመሙ የጠና ከሆነ ወደ ሐኪም ዘንድ መሄድ ግድ ይላል:: አብዛኞቹ የሕክምና ባለሙያዎች ከሚሰጡት ዕውያዊ እገዛ በተጨማሪ «ከወንዶች ጋር ሩካቤ ማድረግ ስትጀምሪ ሕመሙ ይቀንሳል ወይም ይተውሻል» የሚል የመፍትሔ ምክር መደመጡ አይቀርም::

አስቀድሞ በውስጣቸው ከነበረው ተቃራኒ ጾታን የመፈለግ ግፊት በተጨማሪ ይህን ለመሰለ ሕመማቸው ሩካቤ መፈጸም መፍትሔ እንደሆነ ሲነገራቸው ዔሳው «ብኩርናዬ ለኔ ምኔ ናት?» እንዳለ «ድንግናዬ ምን ያደርግልኛል?» በማለት ለዝሙት የተጋለጡም ሰዎች አልጠፉም:: ስለዚህ ይህን የመሰለ ክብር እንድናጣ በብዙ መልኩ መፈተን አይቀርልንም:: ለጊዜው የሚሆን መጠነኛ የሕመም ስሜትን መታገሥ አቅቶን ለማያልፍ ጸጸት አንጋለጥ:: በዚህ መልኩ





እንኳን ሐኪም መክሮን ይቅርና አዘንም ቢሆን ሕገ ወጥ ሩካቤ ማለትም ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ሩካቤን መምከር የለብንም::

ረ. ድንግልና ያላትን ሴት አጭተሃል እንበል:: ምንም ሳትደርስባት ራሳችሁን ጠብቃችው እየኖራችሁ ሳለ በድንገት ተለያያችሁ:: የዚህ ጊዜ ምን ይሰማሃል? ወይኔ ሕንን እንኳን በገሠሥኩ ኖሮ እያልክ ትቆጫለህን? ሊቆጭህ አይገባም! በእርግጥ ይህንን የሚያውቁ ጓደኞችህ አሁን አንተ ወንድ ነህ? እያሉ ሊዘባበቱብህ ይችላሉ:: አንተ ግን መመካት አይገባህም እንጂ ከወንድም ወንድ መሆንህን እመን:: ምክንያቱም ከጋብቻ በፊት ድንግልናን መግሠሥ የዘማውያን ሙያ እንጂ የወንድነት መታወቂያ አይደለም:: እንዲያውም ወንድ የሚያሰኘው ራስን በንጽሕና ለመጠበቅ መቻል ነው::

ደግሞስ አንተን ብቻ ድንግልና ወሳጅ ማን አደረገኽ? አንተ የሷን ድንግልና በምትወስድበት ጊዜና ጎዳና ያንተም ድንግልና እንደሚገሠሥ አታውቅምን? እኔ እንኳን ድንግልናዬን ቀደም አጥፍቼው ነበር ብትል እንኳን ኃጢአት እየሠራኽ መሆኑን ማን በነገረኽ? ዝሙት መሥራት ስልጣኔ፣ ችሎታና ዘመናዊነት አይደለም:: ከሰብአ ትካት፣ ከሰብአ ሰዶምና ከሰብአ ገሞራ ጊዜ ጀምሮ የነበረ ዘማዊነት በምን ምክንያት ስልጣኔና ዘመናዊነት ይሆናል::

ሰ. ሊጋቡ ሲቃረቡ ድንግልናቸውን እንደሚያጡ ሰዎች ሁሉ የተጫጩ ወንድና ሴት የሚለያዩበት ሁኔታም ሲፈጠር ድንግልናቸውን ያጡ ብዙዎች አሉ:: ሁለቱ ተፈቃቃሪዎች ራሳቸውን ጠብቀው ከኖሩ በኋላ የሚያለያያቸው አለመግባባት ሲፈጠር «ንጽሕናቸውን ሳላስፈርስ?» በማለት ሰይጣን በቁጣ ይነሣሣባቸዋል:: ይህ ርኩስ መንፈስ በሁለቱም ወይም ለጥፋት ሐሳቡ በተመቸው

በአንደኛው ያጀርና ሲሆን በውዴታና በማባበል ካልሆነ ደግሞ አስገድዶ በመድፈርም ቢሆን እንዲፈጽመው ሊገፋፋው ይችላል::

ፍቅረኛሞች የሚለያዩበት ጊዜ እጅግ ፈታኝ ወቅት ነው:: ስለዚህ በፍቅር ከሚኖሩበት ጊዜ ይልቅ በሚለያዩበት ጊዜ ንጽሕናን ጠብቆ ለመቆየት የበለጠ ጥንቃቄ ይጠይቃል:: በሚለያዩበት ወቅት ሁለቱም ወይም ከሁለቱ አንዱ መከፋታቸው አይቀርም ስለዚህ እንክብካቤ ባላደርግ «ግፍ» ይሆንብኛል የሚል ሐሳብ ይፈጠርና ቢያንስ አንዱ ወገን መንከባከብ እንዳለበት ይሰማዋል:: የተጎዳን ሰው መንከባከብ ባልከፋ ነበር ነገር ግን መሰናከልና ድንግልናን ማጣት የሚፈጠረው በዚህ የመንከባከብ ሂደት ውስጥ ነው:: ስለዚህ ይህን በመሰለ ጊዜ ጠንቀቅ ማለት ይበጃል::

ከሁሉ የሚያስደንቀውና የሚያሳዝነው እንዲህ ባለ የመለያየት ዋዜማ ፍቅራቸው ለሁልጊዜ መሆኑን የገለጡና ማስታወሻ ያኖሩ እየመሰላቸው ድንግልናቸውን የሚጥሉ ሴቶች መኖራቸው ነው:: አንዳንዶችማ «ለሌላ ከምሰጠው» እስከ ማለት ደርሰው ለሚለያቸው ወንድ ድንግልናቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ:: እንዲህ የምታስቢ ከሆነ እስኪ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ሞክሪ:: እየተለየሽ ያለው ወንድ ኋላ ከምታገቢው ወንድ የበለጠ ተፈቃሪ መሆኑን በምን አረጋገጥሽ? ከበለጠስ ለምን ትለይዋለሽ? ለሚመጣው ባልሽስ ያስቀረሽለት ምን ስጦታ አለሽ? ምን ላድርግለት የሚያሰኝ እጅግ ተወዳጅ ባልስ ብታገኚ የቀድሞ ሥራሽ ጸጸት አያስከትልብሽምን? የምታገቢው ባል ከቀድሞ ፍቅረኛሽና ወደ ፊት ልታገኚው ከምትችይው ማንኛውም ወንድ የበለጠ ልታፈቅሪው ካልቻልሽ ማግባትሽ መቼም ቢሆን ፍጹም ትክክል አይሆንም:: ስለዚህ ድንግልናን ጨምሮ ምርጥ ነገሮች ሁሉ ሊያገባ ላጨሽ ወይም አጭተሽ ለነበረ ሰው ሳይሆን ላገባሽው ወንድ ብቻ መሆን ይኖርበታል:: በተጨማሪም ዝሙት ምጽዋት ሊሆን





እንደማይችል «ዜና ሥላሴ» ይናገራል:: ስለዚህ ዝሙት ሠርተሽ «አሳዝኖኝ ነው!» ብትዪ የሚሰማሽ የለም::

ሸ. የመለያየት ነገር ሲነሣ ሙሉ ለሙሉ ላለመገናኘት የሚደረግ መለያየት ሳይሆን በሥራና በትምህርት ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ ርቆ የመሄድ ዓይነት መለያየት በሚፈጠርበት ጊዜ ወንድና ሴት ተፋቃሪዎች ሩካቤ መፈጸምን ሻይ፣ ቡና እንደ ማለት እየቆጠሩት ይገኛል:: በዚህ ዓይነት አጋጣሚ ክብረ ድንግልናቸውን ያጡ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም:: ይህም ሰው ስለ ድንግልና አጠባበቅ ያለውን የተዛባ አመለካከት ያሳያል::

ቀ. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለ ድንግልናው ያፈረ ሰው ቢኖር» 1ቆሮ7÷36 በድንግልና መኖራቸው የሚያሳፍራቸው፣ ያልሠለጠነ፣ አላዋቂ፣ ጤና ቢስ፣ ወንድነት የሌላቸውና ተፈላጊነትን ያጡ ተደርገው እንደሚቆጠሩ አድርገው ሚያስቡ ብዙዎች አሉ:: እንደዚህ ያሉ ሰዎች ማንኛውም ሰው አብሮአቸው ቢተኛ ተፈላጊነታቸው፣ አዋቂነታቸውና ሥልጡን መሆናቸው የተረጋገጠ ይመስላቸዋል:: ይህ ዓይነቱ ሐሳብ በተገኘው ተራ አጋጣሚ ንጽሕናችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ከማድረግ ያለፈ ፋይዳ የለውም:: ስለሆነም ይህን ከመሰለ ደካማ አመለካከት ተላቆ ንጽሕናን መጠበቅ ተገቢ ነገር ነው::

በ. ሰው ወደዚህ ዓለም ከመጣ ጀምሮ በልዩ ልዩ ጊዜ በተለያየ ደዌ ሲሠቃይ ይታያል:: በዚህ ጊዜ የታመሙትን በሚገባ ማስታመም ለመንግሥተ ሰማይ የሚያበቃ የጽድቅ ሥራ ነው:: ሆኖም አንዳንድ ክፉ መንፈስ ያደረባቸው ሰዎች ታማሚዎችን በማስታመም ሰበብ ዝሙት ሲፈጽሙባቸው መስማት ለጆሮ የሚዘገንን ቢሆንም ይህ

እስነዋሪ ተግባር በተለይየ ጊዜ ተፈጽሟል:: በዚህ ድርጊታቸው ክስ የተመሠረተባቸው ብዙ የሕክምና ባሙያዎችም ይገኛሉ::

እንዲህ ባሉ ቦታዎች የበለጠ ለዝሙት ተግባር የሚያነሣሡ ምክንያቶች አይጠፉም:: አንደኛ ቦታው መጠመቂያ ወይም የሕክምና ቦታ እስከ ሆነ ድረስ ሰዎች ከልብስ ተራቁተው የሚታዩበት ጊዜ አለ:: ሌላው በተለይ በጸበል መጠመቂያ ስፍራዎች ደግሞ ሰይጣን ታማሚዎችን እያወራጨ ከልብስ ያራቁታቸውና አካላቸውን እያዩ ሌሎች በዝሙት እንዲፈተኑ ያደርጋል:: ከዚህም አልፎ ተርፎ ታማሚዎቹን «ሮጠን እናመልጣለን» እያሰኘ ከአስታማሚዎቻቸው ጋር እንዲጓተቱና እንዲታገሉ ያደርጋል:: ታማሚዋና አስታማሚው የተለያየ ፆታ እስካላቸው ድረስ ይህ መላፋት በአስታማሚው ላይ የሚፈጥረው የፍትወት መነሣሣት በምንም ለመመለስ የሚያስቸግር ይሆናል:: ይህን አጋጣሚ እንደ ምቹና እንደ አስደሳች ነገር በመቁጠር ማስታመም ጸጋቸው ሳይሆን ለመላፋትና የሰዎችን ገላ ለመመልከት ከጠበል ስፍራ የማይጠፉ ሰዎች እንዳሉ አስተውለው ያውቃሉ? እንዲህ ከሆነ ከየትም ቦታ ይልቅ በጠበል ቦታዎች በይበልጥ ከሰይጣነ ዝሙት መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ አያጠራጥርም::

ከዚህ በላይ በጣም የሚያሳዝነው ይህ የዝሙት ተግባር በመንፈሳዊነት ሰበብ ሲከናወን ማየት ነው:: ልጸልይልሽ፣ ላስጠምቅሽና ላጥምቅሽ፣ በሚሉ ሰዎች ብዙ ሴቶች ክብራቸውን አጥተዋል:: ይህ የሚሆነው ሰውን ከመጠን በላይ ማመን ሲደራ ነው:: ጉዳዩ መንፈሳዊ መሆኑ ደግሞ ሰዎቹን የበለጠ እንዳይጠራጠሩ ያደርጋል:: ይህን በመሰለ ነገር ብዙዎች ተሰነካክለዋልና አስቀድሞ እንደተገለጸው በሰው ብዙ አለመተማመን መልካም ነው:: ፈዋሽ ጠበል አለ ወደ ተባለበት ቦታ ሁሉ «እግዚአብሔር አለ ምን እሆናለሁ?!» እያሉ ፈጣሪን መፈታተን አይገባም:: ይልቁንም ብዙ





ሰው ወደማይኖርባቸውና በየጫካዎች ወደሚገኙ የጠበል ቦታዎች ጨለማን እንኳን ሳይፈሩ ረጅም መንገድ እጓዛለሁ ማለት እጅግ መታወር ነው:: ከዚህ ቀደም ምንም ጉዳት ባይደርስብን እንኳን ከዚህ በኋላ መሞከር አይኖብንም:: በዚህ ምክንያት ተማሮ ጨርሶ ከቤተ ክርስቲያን ከመራቅ ከወዲሁ መጠንቀቅ ይገባል::

ሌላውን ማስታመም ያንቺን የንጽሕና ኑሮ አደጋ ላይ የሚጥለው ከሆነ አለማስታመም ወይም ታማሚም ብትሆኚ አስታማሚ ማጣትሽ ይመረጣል:: ከሥጋ ሕመም ቅድስናን ማጣት ይከፋልና:: ሰይጣን ዝሙትን ለማስፈጸም ታማሚ ወይም አስታማሚ የሚያደርግበት ጊዜ አለ:: ትዕማር የተባለች የዳዊት ልጅ ድንግልናዋን ያጣችው አምኖንን አስታምማለሁ ብላ ስትንጎዳጎድ ነው:: 2ሳሙ13፥7-17 ይህ ታሪክ ለምን የተጻፈ ይመስልሻል? እግዚአብሔር አንቺን ለማስተማር ፈልጎ አይደለምን? ማስታመም ብቻ ሳይሆን አንቺ ራስሽ ብትታመሚም በምትጎጂበት መንገድ አስታማሚ አትፈልጊ:: አስታማሚ አግኝቶ ንጽሕናን ከማጣት ከነንጽሕና መሞት ይመረጣል:: ብታምኚ ግን እግዚአብሔር አስታማሚ የላትም ብሎ ለሞት አያበቃሽም:: እርግጥ ሕመም መግቢያ ያሳጣልና ወደማንፈልገው ነገር በግድ እንድንገባ የሚያደርግበት ጊዜ አለ:: ሰይጣንም ወጥመዱን በሕመም ምክንያት የሚዘረጋው በዚህ ምክንያት ነው:: ሆኖም ለዘለዓለም ሕይወት የሚበጀውን አውቆ መጠንቀቅና እርምጃ መውሰድ የሰው ፋንታ ነው::

ተ. ሴቶች ድንግልናቸውን እንዳይጠብቁ ለማጥመድ ሰይጣን በዚህ ዓለም የዘራው ብዙ ዓይነት የተሳሳተ አመለካከት አለ:: ከነዚህ ውስጥ አንዱ ሩካቤ ማድረግ በወንዶች ዘንድ ፍቅርን የሚያጸና (መወደድን የሚያመጣ) አድርጎ ማሳሰብ ነው:: ስለዚህ ብዙ ሴቶች ድንግልናቸውን አሳልፈው ላላገቡት ወንድ ይሰጣሉ:: ይህ አስተሳሰብ

አይታጣበትም:: የሚመርጡት የሥራ ዓይነት፣ የሚመኙት ቤትና መኪና፣ የሚሹት ታዋቂነት፣ ዝንባሌያቸው ወዘተ መጨረሻው ከፆታዊ ጉዳይ ጋር ቁርኝት ያለው ሆኖ ይገኛልና ራስን መመርመር ያስፈልጋል::

ነ. ድንግል ነሽ? አይደለሽም? ዓይነት ውርርድና ጨዋታ መቼም ቢሆን የሚያስፈልግ አይደለም:: ወደ ግል ሕይወትሽ የሚያመራ ይህን የመሰል ጨዋታ መሸሽ ይገባሻል:: ለማንም ድንግል ነኝ አትበይ እንዳውም ግድ መናገር ካስፈለገ ሁኔታውን አይቶ ድንግል አይደለሁም ማለት ሳይሻል አይቀርም:: ምክንያቱም ድንግል ነኝ በማለታቸው ብዙዎች ካላሰቡት ወጥመድ ውስጥ ገብተዋልና::

የሚያገባሽ ሆኖ ስለ አኗኗርሽ በግድ ማወቅ ከሚያሻው ሰው በቀር ለማንም ስለ ራስሽ ድንግል መሆንም ሆነ አለመሆን አታውሪ:: ብታወሪ ግን ለጊዜው ሊያኮራሽ ይችል ይሆናል:: ዘግይቶ ግን ሳታዝኝ በት አትቀሪም:: ምክንያቱም ከድንግል ሴት ጋር መተኛት ንጹሕ መሥዋዕት የማቅረብን ያህል የሚያስደስታቸው ሰዎች ብዙ ናቸውና:: ስለዚህ ድንግል ነኝ በማለትሽ በራስሽ ላይ የፈተና ትብትብ ትሸከሚያለሽ::

ሰይጣንም ቢሆን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ደናግላን ክብራቸውን ሲያጡለት ጻድቃንን ያስኮነነ ያህል እጅግ ደስ ይሰኛል:: ስለዚህ ለትዳር ያሰብሽው ሰውም ቢሆን እስከ ጋብቻ ድረስ ከሩካቤ ተጠብቆ መኖር እንደሚገባ የማያምን ሆኖ ካገኘሽው ስለ ድንግልናሽ አታውሪለት:: ብዙ ካጠናሽውና መልካም ሰው ሆኖ ካገኘሽው አንቺ እንኳን ብትሰንፊ እርሱ ሊረዳሽ ይችላልና መጠንቀቅሽ እንዳለ ሆኖ አኗኗርሽን ቢያውቅ መልካም ነው:: ድንግል ሳይሆኑ ድንግል ነኝ





ማለት ይጎዳል እንጂ. ድንግል ሆነው ድንግል መባል አይገባኝም ወይም አይደለሁም ማለት ምንም አይጉዳም::

ኘ. ድንግልና ማጓጓቱ አይቀርም ይልቁንም ድንግል የሆነ ሰው የበለጠ ድንግልን ይፈልጋል:: ታዲያ እንዲህ ዓይነት ሰው ሆነህ ሳለ ተፈትሖ ያገኘት (ድንግል ያልሆነች) ሚስት ብታጭ ሕሊናህ ድንግል ወደ ሆነች ሌላ ሴት እንዳይሳብ መጠንቀቅ አለብህ:: መጀመሪያ ድንግል የሆነች ሴት ብታጭ መልካም ነበር:: ያ ካልሆነ ግን በያዝከው መጽናት አለብህ እንጂ. ከሚስትህ ጋር ክብር በማጣት ለመተካከል ስትል ድንግልናህን ለሌላ አትስጥ:: ወይም ሌላ ድንግልን በመሻት አታመነዝር! ብዙዎች በዚህ ምክንያት ስተዋልና:: ድንግል ሴት አንጉታኽ እንዳታመነዝር ተጠንቀቅ::

አ. ኢዮናዳብ የተባለው ሰው ከትዕማር ጋር እንዲተኛ አምኖንን እንደ መከረው ይህን እንድታደርግ የሚመክሩህ ብዙ ባልንጀሮች ሊኖሩህ ይችላሉ:: ቢሆንም ምክራቸውን በመቀበል ክብርህን መጣልህ ተገቢ አይደለም:: በእንዲህ ዓይነቱ ምክር አምኖንም ቢሆን በሰይፍ ከመገደል በቀር የተጠቀመው ምንም ነገር የለም:: ለሰዎች ግፊት በቀላሉ መረታት አያስፈልግም:: ከሰዎች ግፊት በላይ ደግሞ የመጠጥ ግፊት ተጠቃሽ ነው:: ብዙዎች በመጠጥ ግፊት ንጽሕናቸውን አሳድፈዋል:: ስለዚህ ከዝሙት ለመጠበቅ ከስካር መጠበቅ ዋነኛ መንገድ ነው::

ከ. ለብዙዎች ሰዎች ከክብር ማነስና ለንጽሕናቸው መጉደፍ ሌላው ዓቢይ ተጠቃሽ ነገር ቢኖር ግብዣ ነው:: በልዩ ልዩ ምክንያት የሚከናወኑ የራት ግብዣዎች ብዙዎችን ይህን ለመሰለ ጥፋት ዳርገዋል:: ስለዚህ ይህን በመሰሉ ፖርቲዎች፣ የራት ግብዣዎችና መዝናኛ ፕሮግራሞች ከቻልክ ጨርሶ ተሳታፊ አለመሆን መልካም

ነው:: ካልሆነም እንዴት በጥንቃቄ ራስህን ማስተናገድ እንዳለብህ የራስህን እቅድ ነድፈህ በጊዜ ወደ ቤትህ የምትገባበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርብሃል:: በግብዣው ቦታ ሳለኽም ጥበቃ ባለው መልኩ መንቀሳቀስ፣ ከምታፍረውና ከሚታፈር ሰው ጋር መቀመጥ በእጅጉ ይጠቅማል:: በጣም ማምሸትንና ከቤት ውጭ ማደርን ግን በጭራሽ መሞከር የለብህም:: ይህ የብዙዎች መጥፊያ ሆኗልና::

ወ. ወንድ ከሆንክ ብዙ ጓደኞችህ ሴቶች አይሁኑ:: ይህ ማለት ግን ሴት ጓደኞች አይኑሩህ ማለት አይደለም:: ይልቁኑም ሴቶችን በዙሪያህ አታብዛ ወይም ልክ ሳይኖርህ ወንዶችን የምታቀርበውን ያህል ሴቶችን ምሥጢረኛ አታድርግ ማለት ነው:: ይህ አካሄድ በንጽሕና ለመኖር ለፈለገ ሰው የበለጠ ይጠቅመዋልና::

ሴትም ከሆንሽ እንዲሁ የቅርብ ጓደኞችሽ ወንዶች አይሁኑ:: እንዲያሁም ከብዙ ወንዶች ጋር ያለ ውድ በግድ እንዳትቀራረቢና ክብርሽን ለሚያሳጣ የዝሙት ተግባር እንዳትጋለጪ ተማሪ ሳለሽ እንኳን የምትመርጪው የትምህርት ዘርፍ ወደ ሥራ ዓለም ስትመጪ በይበልጥ የሚያቀራርብሽ ከወንዶች ጋር እንዳይሆን ተጠንቀቂ:: ይህ ሐሳብ የሕይወት ጎዳናን ጠባብ የሚያደርግ ኋላ ቀር ሐሳብ ሊመስል ይችላል:: ሆኖም በንጽሕና መኖር ከምንም ነገር በልጦ የሚታየው ሰው የዚህ ምክር ጥቅም ይገባዋል::

ወንዶችና ሴቶች ባልንጀራሞች ቢሆኑ የሚገኘውን ጥቅም ማንም ይረዳዋል:: ነገር ግን ሴቶች ሴቶችን እየራቁ ከወንዶች ጋር በተወዳጁ ቁጥር የሚያጡትንም ሴትነትና ወንዶችም ሴቶችን ብቻ በመቅረባቸው የሚመጣውን የአርአያ ለውጥ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል:: አንዲት ሴት ሴቶችን እየነቀፈች «ወንዶች ይሻሉኛል» በማለት ብዙ ወንዶችን እጅግ ብትላመድ የሴትነት





መገለጫዎቿን እያጣች ከመሄዷም ሌላ ለዝሙት የተጋለጠች ትሆናለች:: ክብረ ድንግልናዋንም በቀላሉ ታጣለች:: ወንዱም ቢሆን እንዲሁ ነው:: ታዲያ ለተፈጥሮአችን በሚስማማ መልኩ ብዙውን ጊዜ ባልጀሮቻችን ከእኛ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው እንዲሆኑ ለምን ጥረት አናደርግም? በተረፈ ግን የመቀራረባችን ሁኔታ ልክ ይኑረው እንጂ ተቃራኒን ጾታ ባልንጀራ ማድረግ ስሕተት አይደለም::

ዐ. በዚህ ዘመን ንጽሕናውን ጠብቆ መኖር የሚሻ ሰው ራሱን ደብቆ ካልሆነ እጅግ ይቸገራል:: ስለዚህ ሴቶች እኅቶቻችን ከአለባበስ አንሥቶ ትሑት መሆን ይኖርባቸዋል:: ልይ! ልታይ! እና ልወቅ! ልታወቅ! ማለት ድንግልናን ያሳጣል:: ያለ ምክንያትም አደባባይ መውጣትም እንደሁ ነው:: በዚህ ዓይነት አካሄድ ድንግልናን ጠብቆ መኖር እንደማይቻል ማር ይስሐቅ እንዲህ ብሏል:- «ወኢትትዐወቅ ድንግል በውስተ ጉባኤያት ወትዕይንታት» ይህም «ወንዶች መኻል እየዋለች ከተማ እየዞረች በድንግልና የምትገኝ ሴት የለችም» እንደ ማለት ነው:: (ማር.ይስ.አን.28 ምዕ.2) ስለዚህ ክብርን ለማጣት ከሚያጋልጡ ሁኔታዎች አንዱ ወጣ! ወጣ! ማለትና እግርን አለመሰብሰብ ነው ማለት ነው::

## ድንግልና ያስመካል?

ድንግልናን መጠበቅ መልካም ነገር ቢሆንም የሚያመጻድቅና ብዙ የሚያስመካ ግን መሆን የለበትም:: «ድንግል ነኝ እኮ!» ብሎ መመጻደቅ የሚያስከትለው ወቀሳና መዘዝ ድንግልናን ከማጣት በላይ ነው:: አንድ ሰው በድንግልናው የሚመጻደቀው መንፈሳዊነት ሲጎድለውና ዕውቀቱም ያነሰ ሲሆን ነው::

ነቢዩ ኤልያስ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ድንግላዊ ኑሮ ነበረው:: በተጨማሪም ለእግዚአብሔር ቀናዒና ንጹሕ የሆነ አምልኮት የነበረው ታላቅ ነቢይ ነው:: ነገር ግን በዚህ መልኩ የሚኖረው እሱ ብቻ ይመስለው ነበር:: ስለዚህ አንድ ቀን ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር «እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ» ሲል እናነባለን:: ነገር ግን እግዚአብሔር «ከእስራኤል ጉልበታቸውን ለበኣል (ለጣዖት) ያላንበረከኩትን ሁሉ፣ በአፋቸውም ያልሳሙትን ሁሉ ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ::» በማለት መልሶለታል:: 1ነገ19፥14(18)

ዛሬም ቢሆን ደናግላን የሉም ማለት አይቻልም:: ጉልበታቸውን ለዝሙት ያላንበረከኩ የልጅ ፍቅር፣ የሴት ከንፈር ያልማረካቸው ወንዶችና የወንድ ፍቅር ያላገበራቸው ብዙ ሴቶች አሉ:: በንጽሕና ኖረው ለምናኔ፣ ለምንኩስናና የሚበቁ «ሰባት ሺህ» የመንግሥተ ሰማያት ዜጐች ለእግዚአብሔር አሉት:: «ሰባት» ቁጥር በዕብራውያን ፍጹም ቁጥር ነውና፣ «ሰባት ሺህ ዜጎች ለእግዚአብሔር» አሉት ማለት ፍጹም ብዙ ቁጥር ያላቸው ወዳጆች አሉት ማለት ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ በየዘመኑ ብዙ ደናግላን መኖራቸውን ገልጾ ይናገራል:: ለምሳሌ:- «በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨት ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ» ይላል:: ይህን የወንጌላዊ ቃል መምህራን ሲተረጉሙ ብዙ ገሊላዎች አሉና ከእነዚያ ለመለየት «የናዝሬት ከተማ» ሲል ብዙ ዮሴፎች አሉና አረጋዊ ዮሴፍን «ከዳዊት ወገን ለሆነው» በማለት ለይቶ ጠቅሶታል:: በዚያው ዘመን ደግሞ ብዙ ደናግል ነበሩና ከእነዚያ ለመለየት «ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል» በማለት ተናገረ





ይላሉ:: ይህም ትርጓሜ በየዘመኑ ብዙ ደናግላን መኖራቸውን ያስረዳል:: ሉቃ1፥26-27

ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ ይህ ትውልድ ግን ዛሬ ዛሬ ደናግላንን ማግኘት ጭንቅ እንደሆነ ይናገራል:: የዚህ ነገር ዐቢይ ምክንያት ይህ ትውልድ አመንዝራ በመሆኑና ሁሉን የሚመለከተው እንደ ራሱ ስለሆነ ነው:: ይህ ሐሳብ የተጋባባቸው አንዳንድ ደናግላንም ድንግልናቸውን እነሱ ብቻ ጠብቀው እንደሚኖሩ ይሰማቸዋል:: ነገር ግን የሰይጣን ጆሮ ይደፈንና ድንግልናዊ አኗኗርን ከምታወድስ ከቤተ ክርስቲያን ዘልቀው ቢመለከቱ በየጊዜው እንደ ዕንቁ የሚያበሩ ደናግላን ምእመናንን በዐፀዷ ዙሪያ ተኮልኩለው መመልከት ይቻላል:: በዚህ ምክንያት ሰይጣን ብዙ ሴሰኞች ዓይኖቻቸውን በቤተ ክርስቲያን ልጆች ላይ እንዲያነጣጥሩ ማድረጉ ሊታወቅ ይገባል::

ዛሬ ዛሬ ድንግልና የሚገኘው በማዋለጃ ሆስፒታል ውስጥ በሚገኙ ሕፃናት ዘንድ ብቻ እንደሆነ ተደርጎ የሚናኘው ቀልድ መሰል አሉባልታ እጅግ የተጋነነ የሰይጣን ወሬ ነው:: ይህ ዓይነት የተጋነነ ወሬ ድንግልናቸውን ያፈረሱ ሰዎች ከመጸጸትና ንስሐ ከመግባት ይልቅ «በእኔ አልተጀመረ» እያሉ እንዲጽናኑ ሲያደጋቸው፣ ሌሎችን ደግሞ «በድንግልና የምገኝ እኔ ብቻ ነኝ» በማለት በትዕቢት እንዲወድቁ አድርጓቸዋል::

ደናግላን በቁጥር ብዙ መሆናቸው መታወቁ ማንም በድንግልናው እንዳይመካ ያደርጋል:: ብዙ ሰው በያዘው ነገር መመካት አይመችምና:: ከዚህም በተጨማሪ በድንግልናው የሚመካ ሰው ራሱን ቢመረምር እንዳይመካ የሚያደርገውና ለድንግልናዊ ኑሮው የማይስማማ እጅግ በጣም ብዙ የልቡና ርኩሰት ይገኝበታል:: ለምሳሌ:- መመካት፣ በሌላው መፍረድ፣ መታበይ፣ ማማት፣ ክፉ

ፍትወት፣ ሰዶማዊነት፣ ትምክህት የመሳሰሉት ናቸው። ታዲያ ከእነዚህ ሁሉ የረከሱ ሥራዎች ጋር እንደ ትኋን ተጣብቀው እየኖሩ «ድንግል ነኝ እኮ!» እያሉ መመካት አያሳፍርም?

አንዳንዶች ደግሞ በድንግልናቸው ይመኩ እንጂ እነርሱ ራሳቸው በልዩ ልዩ መንገድ ሲያቃልሉት ይገኛሉ። ለምሳሌ:- ድንግልና በገንዘብ የማይተመን ሆኖ ሳለ አንዲት ልጃገረድ «ድንግል ነኝኮ!» እያለች የሚመጣላትን ባል «አንዱን ዕውቀት፣ አንዱን ሹመት፣ አንዱን ገንዘብ፣ አንዱን ንብረት ሌላውን ደግሞ ማራኪ ቁመናና ውበት የለውም» በማለት ከድንግልና ጋር የማይወዳደሩ ነገሮችን ብታማርጥበት ንጽሕናዋን ለተጠቀሱት ነገሮች እንደ መሸጥ አይቆጠርባትምን? ስለ ንጽሕናዋ ንጽሕናን መሻትና መመልከት ሲገባት የሀብትን መጠንና ሌሎች ነገሮችን በማየቷ ድንግልናን እንደሚገባው መጠን ታከብራለች ለማለት አያስደፍርም። ስለ ድንግልና እንዲህ ዓይነት የተዛባ አመለካከት ይዞ በድንግልና መመካት እንዴት ያሳፍራል?

በመጨረሻም ማስተዋል ያለብን ድንግልናችንን ለመጠበቅ የመጀመያዎቹ ተጠቃሾች እኛው ራሳችን ብንሆንም ዐስበ ድንግልናችንን (የድንግልናችንን ዋጋ) ለማግኘት ያህል ነው እንጂ ድንግልናችንን የሚጠብቅልን ራሱ እግዚአብሔር ነው። መጽሐፈ አርጋኖን ስለ መንፈስ ቅዱስ «ንጹሐን ደናግልን ያበረታቸው እርሱ ነው።» ይልና «በድንግልናም ጊዜ የንጽሕና መንፈስ ነው» በማለት ይናገራል። (አርጋኖን ዘእሁድ) ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ደግሞ «እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይደክማል» መዝ126፥1 በማለት ተናግሯል። ትርጓሜውም እግዚአብሔር በከተማ





የሚመሰለውን ሰውነትን በንጽሕና በድንግልና ካልጠበቀ ራሴን ጠብቄ ድንግልናዬን አቆያለው ማለት ከንቱ ድካም ነው ይለናል።

እያንዳንዱ ሰው የግዛ ሕይወቱን ቢመረምር ከላይ የተጠቀሰውን የእግዚአብሐር ጠባቂነት የሚያረጋግጥ ገጠመኝ ይኖረዋል። በዝሙት ለመውደቅ ባለው ኃይል ተጠቅሞ ሲጣጣር፣ ከሰው ሲደበቅ፣ ሠውር ቦታ ሲሻ፣ ምቹ ጊዜ ሲጠባበቅ ባልጠበቀው ሁኔታ እግዚአብሔር ዕቅዱን ያላፈረሰበት ድንግል ነኝ ባይ ከቶ አይገኝም። እንደ ሰውዬው ፈቃደኝነት፣ የልቡና ምኞትና ለዝሙት መዘጋጀት ቢሆን ኖሮ ድንግልናውን ከጊዜያት በፊት ባፈረሰው ነበር። እንደዚህ ከሆነ እግዚአብሔር ጠብቆ ባቆየው ድንግልና መመካት ይገባልን? በጭራሽ ይልቁኑም «ጥበቃውን ከእኔ ያላራቀ እግዚአብሔር ይመስገን» እያሉ ፈጣሪን ማመስገን ለሁሉም የሚገባ ነው።

ከተፈጥሮተ ሥጋ ተፈጥሮተ ነፍስ እንደሚበልጥ ከድንጋሌ ሥጋም ድንጋሌ ነፍስ ይበልጣል። ታዲያ በሥጋ ድንግል መሆናችን ትዕቢትና ትምክህት ፈጥሮ የነፍስ ድንግልና እንዳይኖረን የሚያደርግ ከሆነ እግዚአብሔር ትሑት ሆነን የነፍስ ድንግልናችን እንዲጠበቅልን ለማድረግ የሥጋ ድንግልናችንን በማይረባ ምክንያት እንዲጠፋ ጥበቃውን ከእኛ የሚያርቅበት ጊዜ አለ። እግዚአብሔር «ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣልና» ያዕ4፥6

የሐሳዌ መሢሕ (የሐሰተኛው ክርስቶስ) እናት ከነገደ ዳን የተወለደች ናት። የሐሰት ነቢያት «በድንግልና ፀንሰሽ በድንግልና ትወልጃለሽ» እያሉ ትንቢት ይናገሩላታል። ለጊዜው ድንጋሌ ሥጋ ነበራትና ትዕቢት ያድርባታል። ከዚያ በኋላም ከመቃብረ አረሚ (የአረማዊያን መቃብር) ቆማ ስትጸልይ ከነገደ ዔሳው የተወለደ አንድ ዓይና ጎልማሳ ከወደ ምሥራቅ ይመጣና ከክብር ያሳንሳታል። በዚህ

ጊዜ ፀንሳ ልጅ ትወልዳለች:: አንድ ጊዜ መንፈስ ትዕቢት አድርባታልና በድንግልና ፀንሼ በድንግልና ወለድሁት ትላለች:: ልጇም ተወልዶ ሲያድግ አምላክ ነኝ ፈጣሪ ነኝ ማለት ይጀምራል:: (ራእ13፥1 ትርጓሜ)

ከላይ የተጠቀሰችው የሐሳዊ መሢሕ እናት ገና ለወደፊት የምትመጣ ናት:: ሆኖም ግን ትዕቢቷና ክፉ ግብሯ አስቀድሞ ታውቆ ተገልጧል:: ትዕቢቷና በድንግልናዋ መመካቷ ለመደፈር አበቃት:: ሰው ሲመካ ረድኤተ እግዚአብሔር ይለየዋል:: በዚህ ጊዜ ከላይ እንደ ተጠቀሰችው ሴት ለብዙ ክፉ ነገሮች ይጋለጣል:: አንችም እኅቴ በድንግልናሽ ብትመኪ ዕጣሽ ከዚህ የተለየ አይሆንም:: በድንግልናዋ የምትመካና ድንግል ሳትሆን «ድንግል ነኝ» እያለች የምትዋሽ ሴት ሁሉ በግብርዋ የሐሳዊ መሢሕ እናትን መምሰሏ ጥርጥር የለውም::

እመቤታችን ድንግል ማርያም ግን እጅግ የሚያስደንቅ ትሕትናን ተጐናጽፋ እናያታለን:: ትንቢተ ኢሳይያስን በምታነብበት ጊዜ «እነሆ ድንግል ትፀንሳለች» ከሚለውን አንቀጽ ስትደርስ «አምላክን ለመውለድ ለታደለች ለዚያች ሴት ከዘመንዋ በደረስኩና ወጥቼ ወርጄ ባገለገልኳት ትል ነበር እንጂ እኔ ብሆን ወይም እኔ ነኝ» አላለችም:: በዚህ ሐሳቧና ንግግሯ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴው «ደብር ነባቢት በትሕትና፣ በትሕትና የምትናገር ተራራ» በማለት አወድሿታል:: (ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ዘረቡዕ)

አምላያ ከሌለው ድንግልናና ንጽሕናዋ ጋር ይህን የመሰለ ትሕትና ይዛ በመገኘቷ «ወደ ትሑት፥በቃሌም ወደ ሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ::» ኢሳ66፥2 በማለት የተናገረ እግዚአብሔር በድንግል ማርያም ማኅፀን አደረ:: ድንግል ማርያም ከትሕትናዋ ብዛት የሁሉን ፈጣሪ ከፀነሰች በኋላ እንኳን ስትጸልይ «የባሪያውን ትሕትና





ተመልክቷልና» አለች እንጂ «የእናቱን ትሕትና» አላለችም:: መመካት ቢያስፈልግ ከድንግል ማርያም በቀር የሚያስመካ ድንግልና ያለው የሰው ዘር አልነበረም:: እርሷ ካልተመካች ሊመካ የሚችል ማን ይኖራል? ሉቃ1፥48

በሥጋ ንጽሕናና በድንግልና መመካትና በሌሎች መፍረድ አይገባም:: ይህ ትዕቢት ነውና:: ትላንት በትዕቢታቸው ምክንያት ብዙዎችን ያዋረደና ያሳፈረ እግዚአብሔር ዛሬም በድንግልናቸው የሚመኩትን ሰዎች ብቃታቸው ከራሳቸው እንዳልሆነ ያውቁ ዘንድ በሚያሳፍር ሁኔታ ሊጥላቸው ይቻለዋል:: በድንጋሌ ሥጋ ከሚመካ ትዕቢተኛ ድንጋሌ ሥጋ የሌለው ትሑት ሰው በእጅጉ ይሻላልና መመካት አያስፈልግም::

## ስለ ድንግልና ማልቀስና መጾም ይገባል!

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የተመዘገበለት ዮፍታሔ የተባለው መስፍን አንዲት ሴት ልጅ ነበረችው:: ከእርሷም በቀር ወንድ ወይም ሴት ሌላ ልጅ አልነበረውም:: ይህች ሴት ልጁ ወንድ የማታውቅ ድንግል ነበረች:: በድንግልና ሆና እስከ መጨረሻው ለመኖር ውሳኔ ነበራት::

ከዕለታት በአንድ ቀን ዮፍታሔ ለጦርነት ሲወጣ ጦርነቱን በድል ከፈጸምኩኝና «በደኅና በተመለስኩ ጊዜ ፥ሊገናኘኝ ከቤቴ ደጅ የሚወጣው ማንኛውም ለእግዚአብሔር ይሆናል፣ ለሚቃጠልም መሥዋዕት አቀርበዋለሁ::» ብሎ ለእግዚአብሔር ስእለት ተሳለ ጦርነቱንም በድል በፈጸመ ጊዜ «እነሆም ልጁ ከበሮ ይዛ እየዘፈነች ልትገናኘው ወጣች» ይላል:: እንደ ስእለቱም እርሷን መሠዋት ነበረበትና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይህን አሳወቃት:: በዚህ ጊዜ

ምንም ሳታቅማማ በፍጹም ታዛገርነት «በአፍህ እንደተናገርህ አድርግብኝ» አለችው:: መሳ11፥29-40

ነገር ግን ከመሠዋቷ በፊት አባቷን «ለድንግልናዬ እንዳለቅስ ሁለት ወር አሰናብተኝ» መሳ11፥37 በማለት አባቷን ተማጸነችው፤ አባቷም ፈቀደላት:: ከዚህ በኋላ «በተራሮች ላይ ስለድንግልናዋ አለቀሰች» መሳ11፥29 ይህች ሴት ያለቀሰችው ለምንድር ነው? ምክንያቷ ምንም ይሁን ምን ለእኛ ግን ስለድንግልና ማልቀስ አስተማረችን::

አንቺ ወጣት ሴት ስለ ድንግልናሽ ምን ታስቢያለሽ? እግዚአብሔር ከነድንግልናሽ እንዲጠብቅሽ ጸልየሽ ታውቂያለሽን? ወይስ «እኔን ወንዶች የማይቀርቡኝ ምን አድርገህ ፈጥረኸኝ ነው?» ብለሽ በእግዚአብሔር ላይ ታለቅሺበታለሽ? በድንግልና ሆኖ እግዚአብሔርን ማገልገልስ ታስቦሽ ያውቃል? ቤተሰቦችሽ አንቺን ከአደጋ ለመጠበቅ ሲሉ የሚያደርጉትን ቁጥጥር በምን መልኩ ታይዋለሽ? ይህን አትልበሺ፣ አምሽተሽ አትግቢ የሚል ቁጥጥር እኮ ጭቆና አይደለም:: ነው እንዴ?

ድንግልናን መጠበቅ ብርቱ ትግል ይጠይቃል:: ያ ባይሆን ኖሮ «ድካማቸውን ይቀበል ዘንድ ስለ ደናግል እንማልዳለን» ተብሎ ስለ ደናግል ድካም ባልተጻፈ ነበር:: ታዲያ ይህን ድካም እግዚአብሔር ሳይረዳሽ ትችይዋለሽን? የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት ደግሞ መጸለይ ያስፈልጋል ያውም ከዕንባ ጋር:: (ሥርዓተ ቅዳሴ በእንተ ቅድሳት)

ቤተ ክርስቲያን አንቺን ጨምሮ ስለ ደናግል ሁሉ ትጸልያለች:: ዘወትር በቅዳሴ «እግዚአብሔር የድንግልናቸውን ዋጋ (አክሊል) ይሰጣቸው ዘንድ ለእግዚአብሔር ወንዶችም ሴቶችም ልጆች





ይሆኑ ዘንድ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ስለ ደናግል እንማልዳለን::» ትላለች:: ቤተ ክርስቲያን ስለ አንቺ እየጸለየች" የጉዳዩ ባለቤት አንቺ ግን ባትጸልዩ አሜን ለማለት እንኳን እንደኮራሽ ይቆጠርብሻል::

ፈጣሪ አንድ ቀን ድንግልናችንን በተመለከተ እንድንቆጭ ማድረጉ አይቀርም:: እንዲያገባን የምንቋምጠው ወንድ ካለን ሌላ ነገር ሁሉ ይልቅ ድንግልና ቢኖረን የሚወድ ይሆንና አንድ ቀን እናዝን ይሆናል:: ወይም ሌላ የምንሻቸው ነገሮች ድንግልናችንን ባለመጠበቃችን የተነሣ እናጣቸውና እንቆጫለን:: ለምሳሌ:- በዚህ ምክንያት ለሥርዓተ ተክሊል ወንዶች ደግሞ ለድቁናና ለሌላም መንፈሳዊ ማዕርግ የማንበቃ እንሆንና የምናዝንበት ጊዜ ይኖራል:: ይህ ሁሉ የሚሆነው ድንግልና ያለውን የከበረ ዋጋ እንድናውቅ እግዚአብሔር ስለሚፈልግ ነው:: ክብርን ባለመጠበቅ ምክንያት የሚፈልጉትን ማጣት እጅግ ያሳዝናል:: አያሳዝንም እንዴ?

እርግጥ ነው ድንግልናቸውን ያቃለሉ ሰዎች ስለ ናቁት ድንግልናቸው ምርር ብለው በቁጭት የሚያለቅሱበት ጊዜ ይመጣል:: ይህም ስለ ክብረ ድንግልና ጥልቅ መንፈሳዊ ትምህርት በሚሰሙበት ጊዜ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ከዚያ በፊት ደናግል ሆነው ሳለ እንደ ዮፍታሔ ልጅ ስለ ድንግልናቸው የሚያለቅሱ ሰዎች እንዴት የተመሰገኑ ናቸው? እንደ ዮፍታሔ ልጅ ሁሉ ከማኅበረ ደናግል ተለይታ ወደ ዝሙት ዓለም የገባች አንዲት ሴት ተጸጽታ ስታለቅስ ጓደኞቿም አብረው ያለቅሱላት ነበር:: በኋላም የእርሷና የጓደኞቿ ዕንባ ከበደሏ ጋር ቢመዘን ኀዘኗ በልጦ ስለ ተገኘ በድጋሚ ከመኅበረ ደናግል ገብታ መቆጠሯን ተአምረ ማርያም ይናገራል:: ይህም ስለ ድንግልና ማልቀስ እንደሚገባ ያሳያል:: ደናግላን ክብራቸውን ለማቆየት እያለቀሱ ከዕንባ ጋር መኖር ከተገባቸው ክብራቸውን ያልጠበቁ ሰዎች እንዴት ይልቅ ማዘንና ማልቀስ ይገባቸው ይሆን?

ድንግልናን ጠብቆ ለመቆየት ራስን መግዛት ያስፈልጋል:: ራስን ለመግዛት ደግሞ ጾም ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል:: ስለዚህ ጾምን ጠልቶ ድንግልናን ጠብቆ ማቆየት አዳጋች ነው:: በድንግልናዊ አኗኗራቸው የምናወድሳቸው ቅዱሳን በሙሉ የጾምና የትሕርምት ሰዎች ነበሩ:: ለምሳሌ:- ነቢዩ ኤልያስን ብንወስድ ምንም እህል ሳይቀምስ እስከ አርባ ቀን ድረስ ለመቆየት የቻለ የጾም ሰው እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይተርክልናል:: 1ነገ19÷8

ማር ይስሐቅ «እስመ ጾም ወስኖሙ ለድንግልና ወለቅድስና» ማለትም «የድንግልናና የቅድስና ውበታቸው ጾም ነውና» በማለት ተናግሯል:: ይህም ጾምና ድንግልና ያላቸውን ጥብቅ ዝምድና ያስረዳል:: ቤተ ክርስቲያን «ድካማቸውን ይቀበል ዘንድ» እያለች ስለ ደናግል የምትጸልየው ደናግላን ድንግልናቸውን ጠብቆ ለማቆየት በብዙ ጾም፣ ጸሎትና ስግደት ስለሚደክሙ አይደለምን? ስለዚህ በድንግልና ለመቆየት የሚፈልግ ሰው ጾምን መውደድ አለበት::

## ድንግልናን ማቃለል ያስቀሥፋል!

ድንግልና ወጀብ የበዛበትን የዓለም ባሕር ቀዝፈን የምንሻገርበት መርከብ ነው :: ስለዚህ ድንግልና ከመከራ ይሠውራል:: ድንግል ማርያም ሄሮድስ ሊያደርስባት ካሰበው ኅዘንና መከራ እንዴት እንደዳነች መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንዲህ ይላል:- «ከእባቡም ፊት ርቃ ዘመን÷ ዘመናትም÷ የዘመንም እኩሌታ ወደምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሃ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት::» ራእይ12÷14 እንደሚታወቀው እመቤታችን ከሄሮድስ ፊት ሸሽታ ወደ ግበፅ በረሃ ሄዳለች:: ለዚህም የረዷት ሁለት ክንፎች ንጽሐ ሥጋዋና ንጽሐ ነፍሷ ናቸው::





እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከመከራ የተሠወረችው በንጽሕናዋ ነው:: ንጽሕና ከመከራ ይሠውራልና:: በሁለት ወገን በነፍስና በሥጋ የሚገኝ ድንግልናዋም ሁለት የንሥር ክንፍ ተብሏል፣ ድንግልና ክንፍ ይባላልና:: ስለ ድንግልና ስየሜ በመግቢያ ላይ እንደ ተገለጠው አረጋዊ ዮሴፍ «ኦ ወለተ እስራኤል መኑ ቀረጸ አክናፈ ድንግልናኪ፣ አንቺ የእስራኤል ልጅ የድንግልናሽን ክንፍ ማን ገሠሠው?» በማለት የተናገረው ቃል ድንግልና «ክንፍ» ለመባሉ ምስክር ነው::

ድንግልናን መጠበቅ ከመከራ ከሠወረ ድንግልናን አለመጠበቅ ለመከራ እንደሚያጋልጥ ግልጽ ነው:: ክብርን አለመጠበቅ ያስቀጣል:: ሕግን ያለመጠበቅ የሚያመጣውን ቅጣት ድርሳነ ሚካኤል «ወይ ለክን እሴ ለክን እለ ታማስና ድንግልናክን ዘእንበለ ጊዜሁ እስመ ሀለወክን አፍሐመ እሳት ዘይበልዓክን ዘእንበለ ዓቅም- ድንግልናችሁን ያለ ጊዜው በማይገባ የምታጠፉ እናንተ ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ! እናንተንም የሚበላ የገሃነም እሳት ተዘጋጅቷልና» በማለት ይናገራል:: በገሃነም ከመጣል የሚበልጥ ምን መቅሠፍት አለ? ድንግልናን መጣል በገሃነም ያስጥላል:: (ድርሳነ ሚካኤል ዘጥቅምት)

በእስራኤላዊያን ዘንድ አንዲት ሴት ሳታገባ በአባቷ ቤት ሳለች ድንግልናዋን ብታጠፋ በድንጋይ ተወግራ ትገደል ነበር:: ይህን እንዲፈጽሙ ነቢዩ ሙሴ «ነገሩ እውነት ቢሆን፥ በብላቴናቱም ድንግልናዋ ባይገኝ፥ ብላቴናይቱን ወደ አባቷ ቤት ደጅ ያወጡአት፥ በእስራኤልም ዘንድ የማይገባውን ነገር አድርጋለችና በአባቷም ቤት አመንዝራለችና የከተማዋ ሰዎች እስክትሞት ድረስ በድንጋይ ይወግሩአት፤ እንዲሁም ክፉውን ነገር ከመካከልህ ታስወግዳለህ::» ዘዳ22÷20-21 በማለት አዝዟቸው ነበር:: በዘመነ ኦሪት በሕይወት

ዘመን ለልዩ ልዩ መከራ ከማጋለጥና በኋላም በገሃነም እሳት ከማስኮነን ሌላ ድንግልናን አለመጠበቅ የሚያመጣው ተጨማሪ መቅሠፍት በድንጋይ ተወግሮ መሞት ነበር።

እግዚአብሔር ነገደ ብንያምንም ስለ ክፉ ሥራቸው ለመበቀል ፈልጐ እስራኤላዊያንን ለጦርነት እንዲወጡ ትእዛዝ ባስተላለፈ ጊዜ ከኢያቢስ ገለዓድ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ወደ ምጽጳ ያልወጡ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ባልወጡት ሰዎች ላይ የጉባዔው ውሳኔ «ሂዱ በኢያቢስ ገለአድም ያሉትን ሰዎች ከሴቶችና ከሕፃናት ጋር በሰይፍ ስለት ግደሉ። የምታደርጉትም ይህ ነው። ወንድን ሁሉ ከወንድ ጋር የተኛችይቱንም ሴት ሁሉ ፈጽማችሁ አጥፉ ብለው አዘዟቸው። ወንድ ያላወቁ አራት መቶ ቆነጃጅት ደናግሎች በኢያቢስ ገለዓድ በሚኖሩ መካከል አገኙ፣ በከነዓንም አገር ወዳለችው ወደ ሴሎ ወደ ሰፈሩ አመጡአቸው።» መሳ21፥10-12

ከላይ ከተጻፈው ታሪክ ሕፃናትን ጨምሮ ከወንድ ጋር የተኙና ድንግልናቸውን ያልጠበቁ ሴቶች በሙሉ በሰይፍ ስለት ሲያልቁ ለመዳን የቻሉ ግን አራት መቶ የሚሆኑ ድንግልናቸውን የጠበቁ ቆነጃጅት ብቻ ነበሩ። እነዚህ ከጦርነት መቅሠፍት የተረፉ ደናግላን መዳናቸው ብቻ ሳይበቃቸው መልካም ትዳር ለማግኘት በቅተዋል። ይህም በቁጥር 14 ላይ «ከኢያቢስ ገለዓድም ሴቶች ያዳኗቸውን ሴቶች አገቡአቸው።» በማለት በማያሻማ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ዛሬም ቢሆን ድንግልናን መጠበቅ ከመቅሠፍት ያድናል። ድንግላዊ ካልሆነ በቀር ኤድስን ጨምሮ ከተለያዩ የአባለዘር በሽታዎች ነጻ የመሆን ስሜት የሚሰማው ማን ነው? በዚህ ዘመን ድንግልናን ባልጠበቁ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ያዘዘው መቅሠፍት እንደ ኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ሰይፍ የታጠቁ ወታደሮችን ሳይሆን ልዩ ልዩ ደዌን፣





ሰላም ማጣትን፣ የአእምሮ ጭንቀትን፣ ሥጋትን፣ ግጭትን፣ ጥርጥርን፣ አለመግባባትን፣ መለያየትንና የመሳሰሉትን ነው። እንደ ኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ድንግልናቸውን ያለ ጊዜውና ያለ አግባብ ያጠፉትን ሰዎች የሚቀሥፍ ወታደር (መልአክ) ዛሬም የሚላክ ቢሆን ኖሮ ስንቶቻችን በሕይወት እንተርፍ ነበር? ነገር ግን እግዚአብሔር እንደ ኀጢአታችን አላደረገብንምና ፈጣሪያችን ይክበር ይመስገን!

## ድንግል ሴት ትፈልጋለህ ?

ምንም እንኳን ሰዎች ሁሉም ባይሆኑም ብዙ ሰዎች ግን የሚያገቧት ሴት ድንግል እንድትሆን ይፈልጋሉ። አንዳንዶች ደግሞ መፈለግ ብቻ ሳይሆን የመጀመሪያ መስፈርታቸው ያደርጉታል። ይህ እጅግ ደስ የሚያሰኝ አቋም ነው። ምክንያቱም የሁሉም ሰው አቋም እንዲህ ቢሆን ኖሮ ሴቶች ሁሉ በንጽሕና መኖርን ለወደ ፊት ትዳራቸው መቃናት ሲሉ ስለሚለማመዱት ነው።

ታዲያ ሚስቱ ድንግላዊ ሆና ቢያገኛት የሚመኝ ሰው እርሱም ድንግልናውን የጠበቀ ሆኖ መገኘት እንዳለበት ለአፍታም እንኳ ቢሆን መዘንጋት የለበትም። ስለዚህ ይህን የሚመኝ ራሱን ይጠብቅ። ካላገባሃት ሴት ጋር አንሶላ መጋፈፍን አትሻ። ልታገባ አንድ ቀን የቀረህ ቢሆን እንኳን ሳታገባት ይህን መሞከር የለብህም። በሰዓታትና በቅጽበት ውስጥ በእቅፍህ ያለች እጮኛህ ያንተ ሚስት መሆን የማትችልበት ሁኔታ ይፈጠር እንደ ሆነ አታውቅምና። አንተ ራስህ ከነድንግልናህ የምትፈለግበት ጋብቻ ከፊትህ ይጠብቅሃል። እርሷንም በምትሄድበት ቦታ ባሏ ከነ ሙሉ ክብሯ ይሻታል። ታዲያ ካላገባሃት ሴት ጋር ለምን ትተኛለህ?

ካላገቧት ሴት ጋር ምንጣፍ መጋራት በሰው ቤት መግባትና ከባለ ትዳር ሴት ጋር እንደ ማመንዘር ነው። ያላገባች መሆኗ ልዩነቱ

ባሏን መቀደምህ ብቻ ነው:: አንተ በሰው ትዳር እንዲህ የምትገባ ከሆነ ሌሎች ደግሞ አንተ የምታገባትን ሴት ከክብር አሳንሰው ንጽሕናዋን ገፈው ያቆዩልሃል:: አንተ ድንግል ሳትሆንና የብዙዎችን ሕግ አፍርሰህ ድንግል ሴት መፈለግህ አያስገርምም?

ሰው የራሱን ድንግልና ቢጠብቅ እግዚአብሔር ደግሞ በድንግልና የተጠበቀች ሚስት እንደፍላጎቱ ሊሰጠው ተስፋ ሰጥቷል:: ሰው የራሱን «ዕቃ» ቢጠብቅ ለእርሱ የሚገባውን «ዕቃ» እግዚአብሔር በክብር ይጠብቅለታል:: በመጽሐፍ ቅዱስ «ዕቃ» የሚባለው አባለ ዘርዕ (ኀፍረተ አካል) ነው ቅዱስ ዳዊት «በእውነት ከወጣን ጀምረን እኛ ሰውነታችንን ከሴቶች ሦስት ቀን ጠብቀናል፣ የብላቴኖቻችም ዕቃ የተቀደሰች ናት፣ ስለዚህ ዛሬ ዕቃቸው የተቀደሰች በመሆኗ እንጀራው እንደሚበላ እንጀራ ይሆናል::» 1ሳሙ21፥5 በማለት የተናገረው ቃል ኀፍረተ አካል «ዕቃ» እንደሚባል በሚገባ ያስረዳል::

የራሱን ንጽሕና የጠበቀ ሰው ለእርሱ የምትሆነው ሚስቱ ከነቅድስናዋ፣ ከነንጽሕናዋና ከነሙሉ ክብሯ (ድንግልናዋ) እንደሚያገኛት ማወቅ አለበት ሲል ሐዋርያው «ከእናንተ እንያንዳንዱ የራሱን ዕቃ (ሚስቱ የምትሆነውን) በቅድስናና በክብር (ከነድንግልናዋ) ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ» በማለት ይናገራል:: «ዕቃ» የሚለው ኀፍረተ አካልን መሆኑ ከላይ በማያሻማ መልኩ ተገልጿል:: ስለዚህ ድንግልን ማግባት የሚፈልግ ሰው የራሱን ክብር መጠበቅ ይኖርበታል:: 1ተሰ 4፥5





# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ትውዝፍት (የምንዝር ጌጥ)

እግዚአብሔር የሰው ልጆች እንዲታረዙ (እንዲራቆቱ) አይፈልግም:: ስለዚህ አዳምና ሔዋን ትእዛዙን አፍርሰው የጸጋ ልብሳቸውን በተገፉ ጊዜ «የቁርበት ልብስ አደረገላቸው፤ አለበሳቸውም» ዘፍ3፥21 ነገር ግን ከልክ በላይ ከፍተኛ ዋጋ በማውጣትና ግብረ ገብነት በጎደለው መልኩ ማጌጥ መልበስ የሚያስፈልግበትን ትክክለኛ መንፈሳዊ ትርጉም ያጠፋል::

በልብስ የሚጠቀመው ሥጋ ቢሆንም ልብስ ግን አስፈላጊነቱ ለነፍስ ነው:: ለምሳሌ፦ አንድ ሰው ነፍስ ብትለየው አያፍርም፣ አይለብስም:: ልብስ መግነዝ እንኳን የሚያለብሱት መልበስ ተገቢ መሆኑን የሚያውቁ ነፍስ ያላቸው ሰዎች ናቸው:: ሆኖም በመልበስ ከቁርና ከብርድ የሚድነው ሥጋ በመሆኑ ልብስ ጠቃሚነቱ ለሥጋ እንደ ሆነ ተደርጎ ይነገራል::

ትርጓሜ ወንጌል «ስለነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት ወይም ስለ ሰውነታችው በምትለብሱት አትጨነቁ» የሚለውን ሲተረጉም እንዲህ ይላል፦ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል «ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት አትጨነቁ» ያለው ነፍስ ሥጋዊ መብል የምትበላ ሥጋዊ መጠጥም የምትጠጣ ሆና አይደለም:: ነገር ግን የበሉት የጠጡት ደም ይሆናል (ከሰውነት ጋር ይዋሐዳል):: የበሉት የጠጡት ደም በመሆኑ ደግሞ

ተጠቃሚዋ ነፍስ ናት:: ምክንያቱም «እስመ ነፍስ ተኀድር በደም ፣ ነፍስ በደም ታድራለችና» ተብሎ ተጽፏልና:: ደም ባይኖር ወይም ቢደርቅ ነፍስ በምን ታድራለች? ደም ፈሶ ሲያልቅ ሰው የሚሞተው ነፍስ ማደሪያዋን በማጣቷ ምክንያት ስለምትለይ ነው:: ስለዚህ ተመጋቢው ምንም ሥጋ ቢሆን በዋናነት ተጠቃሚዋ ነፍስ በመሆኗ መብል መጠጥ ለነፍስ እንደሆነ ተደርጎ ይነገራል::

እንደዚሁም ሁሉ ልብስ ለሰውነት (ለሥጋ) ተነግሯል:: በዚህ ትርጓሜ መሠረት ወንጌላዊው «ለነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት ስለ ሰውነታችሁም ደግሞ በምትለብሱት አትጨነቁ» ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው:: ማቴ6÷25 እንኳን ትርፍ ስለ ሆነ ስለ «ማጌጥ» ይቅርና ዕርቃን የሚያስቀር የልብስ እጦት ችግር ቢፈጠር እንኳን «መጨነቅ» እንደማያስፈልግ ይገልጻል::

ስለ አለባበስ ትኩረት ሰጥቶ ማሰብ ባያስነቅፍም መጨነቅ ግን የሚገባ ነገር አይደለም:: «መጨነቅ» ከማሰብ ከፍ ያለ መጠን አልባ ነገር ነው:: ጌታችን በወንጌል «ስለምትልበሱት አትጨነቁ» ብሏል:: ብዙዎች የሚለብሱትን በማጣት ሳይሆን መምረጥ አቅቷቸው ይጨነቃሉ:: ይህ እጅግ የሚያሳዝን ነው:: እንኳን «ያስኬዳል አያስኬድም» እያልን ቀርቶ የምንለብሰው ባይኖረን እንኳን አዳምንና ሔዋንን ቁርበት ያለበስ አምላክ ያለብሰኛል ማለት ይገባናል:: ዘፍ3÷2

ደግሞስ እስራኤላዊያን በምድረ በዳ ለአርባ ዓመታት ሲንከራተቱ «ጫማቸው ሳይፈታ፣ በትራቸው ሳይወድቅ፣ ልብሳቸው ሳያልቅ» ያኖራቸው እግዚአብሔር አይደለምን? ስለዚህ እስራኤል ዘነፍስ የተባልኩኝ እኔንም አይተወኝም ማለት እንዴት ያቅተኛል?





ይብላኝ እንጂ ለእኔ እምነት ለጎደለኝ «የሜዳ አበቦችን የሚያለብሳቸው» እርሱ እኔን ማልበስ አይሳነውም:: ማቴ6÷28 በእምነት ጠንክሬ እንደ ቅዱስ ዳዊት «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝም የለም» እያልኩኝ የምዘምረው መቼ ይሆን? መዝ 22፣1 እንደ ቅዱስ ጳውሎስስ «ምግብና ልብስ ከኖረን ግን እርሱ ይበቃናል» በማለት ለመመስከር እበቃ ይሆን? 1ጢሞ6÷8

## የሰው ነፍስ ስለ አለባበስ በቂ ግንዛቤ አላት!

ልብስ የሚያስፈልግው ለነፍስ እስከ ሆነ ድረስ ነፍስ ስለ ልብስ ማንም ሳያስተምራት በደንብ ታውቃለች:: አዳምና ሔዋን ጸጋቸው በተገፈፈ ጊዜ «የበለስ ቅጠሎችን ቆርጠው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ» ይህን ማን አስተምሮቸው ነው? ነፍስ መልበስ እንደሚገባ ስለምታውቅ አይደለምን? ዘፍ3÷7 ከዚህ አንቀጽ ሳንዘል ነፍስ ስለ ልብስ ያላትን ግንዛቤ በሚገባ መመርመር ይኖርብናል:: ምክንያቱም ነፍስ ልብስ አስፈላጊ መሆኑን ብቻ ሳይሆን መልበስ ያለብንን የልብስ ዓይነትና በዋናነት መሸፈን የሚገባውን የአካል ክፍል ለይታ ማወቋን ይጠቁመናልና::

በዘመነ አዳም ሌሎች ፍጥረታት፣ ለምሳሌ፡ እንስሳት ልብስ አልለበሱም ነበር:: አዳምና ሔዋን ግን ለራሳቸው «አገለደሙ» እንጂ እነርሱን አይተው እኛም መልበስ አያስፈልገንም አላሉም:: ከሁሉ የሚደንቀው ደግሞ ብዙ ዕፀዋት እያሉ ከእነዚያ መካከል በለስን መምረጣቸው ሳያንስ ያን ሰፍተው ማገልደማቸው ነው:: የለበሱት ብርድን ለመከላከል ብቻ ቢሆን ኖሮ ከማገልደም ይልቅ ሌላ አካላቸውንም ጨምረው ባለበሱ ነበር:: ነገር ግን ነፍስ ቅድሚያ መልበስ ያለበትንም አካል ታውቃለችና «አገልደሙ» እንጂ ሙሉ

ለሙሉ አልለበሱም:: ልብሳቸው የበለስ ቅጠል ሆኖ በመቸገራቸው እንጂ ከወሊድ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ሕዋሳቶቻቸውንም ጨምረው ይሸፍኑ እንደ ነበር ጥርጥር የለውም:: ነገር ግን ከነበረባቸው የልብስ ችግርና ማንም ሳይመክራቸው እንዲህ ማድረጋቸውም ለኛ ብዙ ትምህርት ያስጨብጠናል:: አካላቸውን የሸፈኑት በለስ እስከ መስፋት ተቸግረው ነውና:: እኅቴ ሆይ እስኪ ልጠይቅሽ! አንቺ ይህን ያህል ተቸግረሽ ሰውነትሽን ለመሸፈን ትጥሪያለሽ? ወይስ የሚያስጨንቅሽ ሕዋሳቶችሽን በዘዴ አጋልጦ ሌሎች እንዲያዩሽ ለማድረግ አለመቻልሽ ነው?

አዳምና ሔዋን ማገልደማቸው ብቻ በቂ አለመሆኑን ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር የቁርበት ልብስ እንዲለብሱ በማድረጉ አስረድቶናል:: መጽሐፍ ቅዱስ «አለበሳቸው» ይላል እንጂ ግልድም ሰጣቸው አይልም:: እኛንም ግልድማችንን አስወልቆ እንደ እነርሱ ያልብሰን:: አሜን! ዘፍ3፥21

ከአዳምና ከሔዋን ታሪክ ሌላም ቁም ነገር እንማራለን:: ሰው ምን ዓይነት ልብስ መልበስ እንዳለበት ሌላውን ሰው መጠየቅ አይኖርበትም:: ከዚህ ይልቅ ራሱን ይመርምር፣ ነፍሱንም ይጠይቅ:: ሕሊናውን የሚሰማ ከሆነ በቂ መልስ ያገኛል:: ብዙ እኅቶች ግን ስሜታቸውን እንጂ የነፍሳቸውን ፈቃድ አይከተሉም:: ሆኖም ነፍስ መሆን ያለበትን መጠቆሟን፣ መንፈስ ቅዱስም «በማይገባ ልብስ» ስንሸለም መውቀሱን ስለማይተው ሴቶቻችን የለበሱት ተገቢ ልብስ አለመሆኑ ይታወቅ ዘንድ ሲያፍሩ፣ አጠረ ብለው የለበሱትን ሲጎትቱና ወይም በልዩ ልዩ ዘዴ የተራቆተውን የሰውነት ክፍል





ለመሸፈን ሲሞክሩ ይታያሉ:: ከዚህ ሁሉ ግን ይበልጥ የሚጠቅመው የነፍስን ፈቃድ አዳምጦ ተገቢ ልብስ መልበስ ነበር::

## አለባበስን በተመለከተ ስለ ወንዶችስ ምን ሊባል ይችላል?

አለባበስን በተመለከተ ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: ሠለስቱ ምዕት በሃይማኖተ አበው «ወይኩን አልባሲከ በተዓቅቦ፣ አለባበስህ በጥንቃቄ ይሁን» በማለት አዘዋል:: ሊቃውንት አባቶቻችን አሁንም በሃይማኖተ አበው የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ «ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው::» ራእይ16፥15 በማለት የተናገረውን ምሥጢሩ ብዙ ኃይለ ቃል ዋቢ በማድረግ እነርሱም «ወዓዲ ተዐቀብ ከመ ኢትትዐረቅ እምልብስከ ቅድመ መኑሂ ዘእንበለ ዳዕሙ ሰበ ይረክበከ ምክንያት ለተዐርቆ» ብለዋል:: ይህም በአማርኛ «ዳግመኛ በማንም ፊት ከልብስህ ራቁትህን እንዳትሆን ተጠበቅ የምትራቆትበት ምክንያት ቢያገኝህ ነው እንጂ::» ተብሎ ይተረጎማል:: ስለዚህ በሐኪም ፊት እንድንራቆት የሚያደርግ በሽታን የመሰለ ነገር ሳያገኝን ተራቁቶ መታየት ያስጠይቃል::

የኖኅ መራቆት የልጅ ልጁን ከነዓንን ለእርግማን ዳርጓል:: ዘፍ8፥22-25 የቤርሳቤህ ከልብስ ተራቁቶ መታየት ራሷንና ዳዊትን ለዝሙት ዳርጓል:: 2ሳሙ11፥2-4 ስለዚህ መራቆት የማያስፈልገው በቤተሰብም ሆነ በተመሳሳይ ፆታዎች መኻል ነው እንጂ ዘመድ ባልሆንና በሩቅ ሰው ዘንድ ብቻ አይደለም::

ለክህነት ራሳችንን ለየን እንጂ እንደ ወታደርም የጦር ሥራ ለመሥራት የምንችል ነን ለማለት ነው:: ስለዚህ ልብስ የሰው የሥራውና የተፈጥሮው ልዩነት መታወቂያ ነው እንጂ ነፋስና ብርድን መከላከያ ብቻ ወይም የፋሽን ገበያ ማሞቂያ አይደለም:: እንዲህ ከሆነ ክርስቲያኖች የልብሳቸውን አርአያ እንደፈለጉ ከመቀያየር ተቆጥበው በሥርዓትና በአግባቡ ማጌጥ አለባቸው::

## «የሚገባ ልብስ»

ክርስቲያኖች ሊለብሱት የሚገባና የማይገባ የልብስ ዓይነት አለ:: ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ «ሴቶች *በሚገባ ልብስ* ከእፍረትና ራስን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ::» በማለት የተናገረው ቃል ምስክር ነው:: 1ጢሞ2÷10

የማይገባ ልብስ የሚባለው አካልን ለእይታ የሚያጋልጥና ፀረ ክርስትና መልእክት ያለው ልብስ ሁሉ ነው:: በላዩ ላይ የዝሙት መልእክት ያለው ሥዕልና ጽሑፍ ያዘለ ከሆነ፣ ስስና ዘርዛራ ወይም ከገላ ጋር የሚጣበቅ ሆኖ ገላን የሚያሳይና ቅርጽን የሚያወጣ ከሆነ ወይም በማናቸውም መልኩ ክርስቲያናዊ ዓላማን የሚፃረር ከሆነ ክርስቲያኖች ሊለብሱት አይገባም::

የማይገባ አለባበስ የሚባለው የሴቶች ሱሪ መልበስ ብቻ አይደለም:: ቀሚስም የማይገባ ልብስ ሆኖ የሚገኝበት ብዙ መንገድ አለ:: ለምሳሌ እጅግ ቢያጥር ወይም ተሰንጥቆና ሳስቶ ሰውነትን ለእይታ ካጋለጠ ቀሚስ በመሆኑ ብቻ «የሚገባ ልብስ» ሊሆን አይችልም::





አንዲት ልጃገረድ ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ በሰውነቷ ላይ የሚታየው ለውጥ ለአቅመ አዳም የደረሱ ወንዶችን በኃይል የሚማርክ ይሆናል:: በዚህ ምክንያት ሴቶች በወንዶች በተደጋጋሚ ይፈተናሉ:: አንቺም ወደ ትልቅ ሴትነት ስትቀርቢ ተመሳሳይ የሆነ ፈተና ያጋጥምሻል:: እውነተኛ የልብና የሕሊና ሰላም ለማግኘትና ዘለቄታዊ ሰላምሽን የሚያደፈርሱ ችግሮች እንዳይደርሱብሽ የምትፈልጊ ከሆነ ራስሽን መቆጣጠርና ትክክኛ ለሆነው ነገር ጠንካራ አቋም ማሳየት ይጠበቅብሻል::

ከወሊድ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን የሰውነትሽን ክፍሎች ለማሳየት ቁምጣና አጣብቂኝ የሆኑ ጉርድ ቀሚሶችን፣ አጭር ቀሚስና ጠባብ ሹራቦችን፣ ስስና ዘርዛራ ልብስ፣ ጠባቃ ሱሪ፣ እየለበስሽ ሆን ብለሽ ትኩረት መሳብ ይገባሻልን? እንዲህ ያደረግሽ እንደሆነ የወጣት ሴቶች ፆር በሆነው የምንዝር ጌጥ ፍቅር (ትውዝፍት) ተይዘሻል ማለት ነው:: በዚህ መቀጠልሽ ደግሞ የተቃራኒ ጾታዎችን ፍትወተ ሥጋ የመቀስቀስ ሚና ይጫወታል:: ከዚያስ በኋላ ምን እንደሚከተል ታውቂያለሽ?

በዚህ ዓይነት አድራጎትሽ የተሳቡ ወንዶች የሚያቀርቡልሽን ፈተና ሁሉ ለመቋቋም ምን ያህል ችሎታ አለሽ? ፈተናው እንደ ስኳር በሚጣፍጥ ወይም ሥውር በሆነ ማባበልና ማታለል፣ በውዴታ፣ ገፋ ካለም በግዴታ ሊሆን ይችላል:: ታዲያ ገና በማደግ ላይ ያለሽ ስትሆኚ ይህን ሁሉ እንዴት ችለሽ ታልፊዋለሽ? አካላዊ ዕድገት አሳይተሽ ይሆናል ፤ ነገር ግን ምን ያህል ለጋብቻና እናት ለመሆን የሚያስፈልገው የአእምሮና የስሜት ብስለት አለሽ? በአካል ማደግሽ ብቻ በቂ አይደለም::

ዕድገቱን የጨረሰ ነገር ግን ያልበሰለ አረንጓዴ ሙዝ አይተሽ ታውቂ ይሆናል:: ይህ ሙዝ ከተቆረጠ በኋላ እንኳን ለመበላት ገና መብሰል እደሚያስፈልገው አታውቂምን? አንቺም እንዲሁ በአካል የደረስሽ ቢመስልሽም ይህን ለመሰለ ጾታዊ ግንኙነት ለመጀመር ገና መብሰል እንደሚቀርሽ ራስሽን አሳምኚው:: ብትጣደፊ ግን ጊዜው ሳይደርስ የጽጌሬዳን እንቡጥ ለመክፈት እንደ መሞከር ይሆንብሻል:: ይህም ትርፉ አበባን ማበላሸትና ወደ ፊት ሊገኝ የሚችለውን ውበት መጉዳት ብቻ ነው::

ጋብቻ ማለት ሙሽራ መሆን ብቻ እንዳልሆነም አትዘንጊ የቤት አደራጅ፣ ምግብ አዘጋጅና ልብስ አጣቢ መሆንንም ያካትታል:: እናት መሆንም ልጆችን ተንከባክቦ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ትዕግሥትና ጽናት የሚጠይቅ ነው:: ይህ ሁሉ ደግሞ በጥሩ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በክፉ ጊዜም በሕመምና በጤንነት ጊዜ ሁሉ ጭምር ሳይቋረጥ መደረግ የሚያስፈልገው የሕይወት እንቅስቃሴ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ለጋብቻ ዝግጁ እንደሆንሽ ቢሰማሽ እንኳን ልታገቢው የምትፈልጊው ምን ዓይነት ባልን ነው? አንድ ወጣት ወንድ የተማረከው አንዲት ልጃገረድ በጾታ ግንኙነት በኩል ልትሰጠው በምትችለው እርካታ ላይ ብቻ በማተኮር ከሆነ ጥሩ ባል የሚሆን ይመስልሻል? ታዲያ ሰውን በአለባበስና በውጫዊ ውበት ለመማረክ ከመሞከር ይልቅ ውስጣዊ ማንነትሽን ተመልክቶ ማለትም በአእምሮሽና በልብሽ ውስጥ ያለውን አይቶ ዘላቂ ወዳጅነት እንዲመሠረት ብትፈልጊ በጣም የተሻለ አይመስልሽምን? ይህን ለማድረግ የምትችዪው ደግሞ ለአለባበስሽ ከመጠን በላይ ከመጨነቅ





ይልቅ ሌሎችን የሚስቡ መልካም ጠባዮችን በማፍራት ነው:: ማለትም በግልጽና በበሳል አነጋገር፣ ስለ ሕይወት ባለሽ ደስተኛና ጤናማ አመለካከት፣ እንደዚሁም ለታማኝነት፣ ለግብረ ገብነት፣ እግዚአብሔርን ለመፍራትና ለመሳሰሉ መልካም ነገሮች ያለሽን በጎ ፍላጎት በቃልና በሥራ ለማሳየት በመጣር ነው::

ከዚህ አልፈሽ የትዳር ዓላማ ሳይኖርሽ መረን በወጣ የዝሙት ተግባር ለመኖር አስበሽ አለባበስሽን ያበላሸሽ ከሆነ ዘግየት ብሎ ማዘንሽ አይቀርም:: አለባበሳችን ኑሮአችንን ደስተኛ ወይም ኀዘን ያጠላበት ለማድረግ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው:: ደስተኛና መልካም ስብእና የሞላበት ኑሮ ለመኖር የሚደረግ ጥረት አለባበስን ቁጥብ ከማድረግ ይጀምራል:: አስተውሎ መልበስ የመልካም ስብእና መገለጫ ሲሆን ስድ አለባበስ የሚፈጥረውን የስሜት መገለባበጥ መሠረት ያደረገ የአኗኗር መንገድን መከተል ከሰውነት ደረጃ ዝቅ ያደርጋል::

ስለዚህ ሆን ብለሽ ጥፋትን ዓላማ ያደረገ አለባበስ ከመልበስ ተጠንቀቂ! በአለባበስሽ አንድን ወንድ ብትማርኪ አንቺም ሆንሽ እርሱ አትደነቁም:: ምክንያቱም እርሱ በእንስሳዊ ጠባይ የሚማረክ ደካማ ሲሆን አንቺም ደግሞ በስሜት ብቻ እንጂ በውስጣዊ ማንነትሽ በአእምሮአቸው በሳል የሆኑ ሰዎችን መማረክ ያቃተሽ ደካማ ነሽና:: ጎበዝ ከሆንሽ ከስሜት ይልቅ በበሳል አስተሳሰብና በጨዋነት የሚሳቡትን ሰዎች ለመማረክ ጨዋና ግብረ ገብነት ያለው ሰው ለምን አትሆኚም?

በወጣትነትሽ ለፈጣሪሽ ታማኝ ሁኚ! ለውጫዊና ለጊዜያዊ ደስታ ብለሽ መልካም ጠባያትን ንቀሽ አትጣያቸው:: ውስጣዊውን

ንቀሽ ለሥጋዊና ለውጫዊ ነገሮች ተገዝተሽ መኖርሽ ከፈጣሪሽ ጋር በእጅጉ ያራርቅሻል። እርሱ እንዲህ ብሏልና «በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሠወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ» 1ጴጥ3÷4 ስለዚህ ስለውስጣዊ ማንነትሽ እንጂ ስለውጫዊው ማንነትሽ ብዙም አትጨነቂ።

## በአልባሳት በምታጌጪበት ጊዜ ልታስተውያቸው የሚገቡ ነገሮች!

ሀ. ወጣት በምትሆኚበት ጊዜ ስለ አለባበስሽና ስለ ውጫዊ ማንነትሽ የምትጨነቂው በአብዛኛው እኩዮችሽ ስለ አንቺ ምን እንደሚያስቡ በማሰብ ነው። በዚህ ጉዳይ ብዙ አትልፊ እነርሱ ራሳቸው በመለወጥ ላይ ያሉ ገና ታዳጊዎች መሆናቸውን መዘንጋት የለብሽም። ስለዚህ ዛሬ በአድራጎትሽ ቢደሰቱ ነገ በጭራሽ ላይደሰቱ ይልቁንም ነገሮች ሲገቧቸው ባሳደርሽባቸው ተጽዕኖ ሊያዝኑብሽም ይችላሉ።

እኩዮችሽን ያስደስታል ብለሽ የምታደርጊው ነገር ወላጆችሽንና በአንቺ ግምት የምታከብሪያቸውን፣ የምታደንቂያቸውንና ከፍ አድርገሽ የምትመለከቻቸውን ሰዎች በእጅጉ ሊያሳዝናቸው ይችላል። ለምን ቢባል ከእኩዮችሽ ይልቅ አድራጎትሽ የሚያስከትለውን ቀውስ መመርመር ስለሚችሉ ነው። በወላጆሽና እንደነዚህ ባሉ ሰዎች ዘንድ ዝቅ ተደርገሽ እንዳትታዪና እንደ ትልቅ ሴት እንድትቆጠሪ ከፈለግሽ ከአለባበስሽ ይልቅ ስለመልካም ሴትነትሽ ተጨነቂ።





ለ. ሴቶች ያገቡ ወይም ያጩ ከሆነ ልብስ በሚለብሱበት ጊዜ ስለ ትዳራቸው በትኩረት ማሰብ ይኖርባቸዋል። ልብስ ከግብረ ዝሙት ጋር የጠበቀ ትስስር ስላለው ባሎች የሚስቶቻቸውን አለባበስ በጥንቃቄ ይከታተላሉ። ለአፋቸው ልበሺው «ያምርብሻል» ቢሉም እንኳን ሚስቶች ለባሎቻቸው ሐሊና መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። ይህን ችል ብላ የምታልፍ ሴት የገዛ ትዳሯን በራሷ እጅ እያፈረሰች መሆኗን ማወቅ አለባት። ምክንያቱም የሴቶች አለባበስ በወንዶች ስሜት ላይ ያለውን ሚና ወንዶች ከራሳቸው በመነሣት በሚገባ ስለሚያውቁ ያንቺ አለባበስ የሚያስከትለውን መዘዝ ለመገመት ለባልሽ በጣም ይቀለዋል።

ባልሽን ለምን ቅናት ታስተምሪዋለሽ? ቅናቱ በጨመረ ቁጥር የበለጠ የምትቸገሪው አንቺ መሆንሽን አታውቂምን? ምንም አልተናገረሽም ማለት አለባበስሽን ወዶልሻል ማለት አይደለም። የባልን ስሜት የሚጎዳ አለባበስን ለይቶ ለማወቅ መራቀቅ ወይም ባል እስኪናገር መጠበቅ አያስፈልግም። በእርግጥ ባል ስሜቱን የሚነካ ዓይነት አለባበስ ሚስቱ ስትለብስ የተሰማውን ስሜት ገልጾ የመናገር ኃላፊነት አለበት። ቢሆንም ግን ሆን ብላ ካልሆነ በቀር ባሏ የማይወደውን የአለባበስ መንገድ ለይታ የማታውቅ ሴት አለች ለማለት ያስቸግራል።

ሚስቶች አለባበስን በተመለከተ የራሳቸውን ስሜት ብቻ ሳይሆን የባሎቻቸውንም ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተናግሯል። በሚስቶች ተገቢ ያልሆነ አለባበስ ባሎች የሚሰማቸውን ሲናገርም «ወሶበሂ አ.ነፈረ ነቢበ እንበይነ ንጽሑ ዘእንበለ ጻእሙ ይትሐዘበኒ በልቡ።

ወታመጽኢ ቅንአተ በርእስኪ:: ወታኅጥኢ ኩሎ ተድላ በእንቲአሁ:: ወባሕቱ ትጻልኢ:: ወትሴስሊ እምኔሁ::» ይህም «በማይገባ ልብስ አጊጠሽ ባየ ጊዜ ሐኔ ይፈርስብኛል ብሎ ሊናገርሽ ቢያፍር እንኳን በልቡ ይጠረጥርሻል:: በሥራሽ ቅንአትን ታመጭበታለሽ:: ስለ ቀናም ከእርሱ የምታገኚውን ተድላ ታጫለሽ:: ትነቀፊያለሽ ስለዚህ ከባልሽ ተፋተሽ ትሔጃለሽ» ማለት ነው:: ዳግምኛም በልብሰ ዘማ አጊጣ ስትወጣ ባያት ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን የምትሔድ እንኳን ቢሆን «ባይከለክላት እንኳን ይጠረጥራት የለምን? ከቤት ሳለች እንዲህ የማታጌጠው ለምንድር ነው? ምን አምሯት ይሆን?» ማለቱ አይቀርም:: ይህም ቃል በግእዙ እንዲህ ይነበባል፦ «ወእምኒ ኢከልአ አኮኑ እምተሐዘባ:: ወይቤ ለምንት ኢትሠረገው ውስተ ቤት ወኢትሤነይ:: ወምንትኑ መፍቅዳ::» (ተግ.ዘዮሐ 28)

ሐ. «እኔ እንዲህ የማጌጠው ባሌ ውጭ ውጭ እንዳይልብኝ ነው!» በማለት ልብሰ ዘማ (የዘማዊያንን ልብስ) መልበስ አትለማመጂ:: ከዚያ ይልቅ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ተናገረው «ንጹሑን ኑሮሽን እየተመለከተ» ባልሽ ባንቺ እንዲማረክ አድርጊ:: 1ጴጥ3÷1-6 ባልሽን በአለባበስሽ እንዲማረክ ማድረግ የበለጠ ሴሰኛ ማድረግ መሆኑን አታውቂምን? ባልሽ «ንጹሕ» ሰው ከሆነ የሚማረከው በ«ንጹሕ» አኗኗርሽ እንጂ በአለባበስሽ አይደለም:: «ወእመሰ ተሠርገውኪ በዘዚአሁ ሥርጉ ወኮነ ምትኪ ዘማዌ የሐውር ኀበ ካልእት»ማለትም «ባልሽ ሴሰኛ ከሆነ ግን ምንም በጌጦች ዓይነት ሁሉ ብታጌጪ ካንቺ ወደ ሌላ መሄዱ አይቀርም::» ምክንያቱም በማጌጥ ካንዷ ሴት አንዷ መብለጧ አይቀርምና:: (ተግ.ዘዮሐ 28)





መ. ከወሊድ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን አካላት የሚያጋልጥ ልብስ ለብሶ ወደ ገበያና ሥራ ቦታ መሄድ እጅግ ያሳፍራል:: ለሥራም የሚመች አይደለም:: ይልቁኑም ለክርስቲያኖች ሰውነትን እንደ ኩበት የሚያስገምት ልብስ ለብሶ በመዋኛና በመታጠቢያ ስፍራዎች ወዲህና ወዲያ ማለት እንዴት ያስነውራል? ከዚህ ሁሉ ግን የሚያስወቅሰው በልብሰ ዘማ አጊጦና ተገላልጦ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ «ቦኑ ትትቃወሚዮ ለቃለ ሐዋርያ ብፁዕ ጳውሎስ» በማለት እንደ ተናገረው ወደ ቤተ ክርስቲያን የምትሔጂው «ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ራስዋን ታዋርዳለች» በማለት የተናገረውን ቅዱስ ጳውሎስን ለመቃወም ነውን? 1ቆሮ11÷5

ሠ. የማይገባ አለባበስ በክርስቲያኖች ዘንድ ቢታይ በማያምኑ ሰዎች ፈጣሪያቸውን ያሰድቡታል:: ለምሳሌ፦ አንዲት ሴት እጅግ በጣም ከፍተኛ ዋጋ በሚያወጣ ልብስ ተሸልማ የሚበሉትና የሚጠጡትን አጥተው የተቸገሩ ድሆች ቢያይዋት ስለ ፈጣሪ የሚያስቡት ምንድር ነው? «እኛ እንዲህ ስንቸገር አንተ ሰብስበህ ለአንዲቱ ይህን ሁሉ ታሸክማታለህን? አንተንስ ፋንድያ ማጠን ነው!» አይሉትምን? እንዲህም ባይሉት ፈጣሪ የማይወዳቸው እየመሰላቸው ተስፋ መቁረጣቸው አይቀርም:: አሕዛብንም ቢሆን ግብረ ገብነት የጎደለው አለባበሳችን ወደ ሃይማኖታችን እንዳይሳቡ ሊያደርጋቸው ይችላል::

ረ. አለባበስን በተመለከተ የራስን ስሜት፣ የትዳራችንን ሁኔታ፣ የድሆችንና የማያምኑ ሰዎችን ሕሊና ላለመጉዳት ከማሰብ በላይ ከፈጣሪ ሕግ ላለመውጣት ጥረት ብናደርግ አለባበሳችን በዘመናችን ሁሉ ብዙ እጅግ በጣም ተለዋዋጭ እንዳይሆን ለማድረግ ባልቸገረንም